ማውጫ /Contents/

Birritu is a quarterly magazine published by:

The National Bank of Ethiopia. It presents indepth articles, features and news on banking, Insurance and micro-finance.

Birritu No. 104

Board chairman:
Gebreyesus Gunte

Members:
Alemayehu Kebede
Getahun Nana
Yewondwossen Eteffa
Teffera lemma

Deputy Editors in-chief:
Bekalu Ayalew
Mulugeta Ayalew

Secretarial and distribution service:
Kelemework Kidane

Address:
Birritu Editorial Office
P.O.Box: 5550Addis Ababa, Ethiopia
Tel: 251-011-553 00 40
251-011-551 00 60
Addis Ababa, Ethiopia
Birritu@ethionet.et

1. የአዘጋጆች ማስታወሻ **(Note from the Editors)** 2

2. ዜና እና መረጃዎጪ **(News and Information)** **3**

3. ጥናታዊ ፅሑፎች **(Researches)**

- Determinants of International Tourism Flows to Ethiopia 5
- ትምህርታዊ ጽሑፎች(Educational Articles)
- የአሜሪካ የፋይናንስ ሥርዓት ቀውስ መንስዔዎች የመፍትሔ ሃሳቦችና በኢትዮጵያ ላይ የሚኖረው እንድምታ 12
- የሥራ ውጥረት መንስኤዎችና ቁጥጥራቸው 19

4. Myscellany

- ረዣዥም ጫፎች 31
- The NBE Commitment 41
- እንተላለፍ 43
- FAQ 44

OPINIONS EXPRESSED IN ARTICLES DO NOT NECESSARILY REFLECT THE POLICIES AND STANDS OF THE NATIONAL BANK OF ETHIOPIA.

FOR RESOURCES, PLEASE VISIT THE NBE's OFFICIAL WEBSITE:

www.nbe.gov.et

Note from the Editors

As customary, this issue also came up with news and information, educational and literary pieces. In our news & Information column, the revised and recently ratified proclamation by the Council of Ministers, that governs the NBE's employees, is entertained among others.

The second part of the Magazine presents a research paper entitled "Determinants of International Tourism Inflows to Ethiopia,". The causes of the recent financial crisis in USA, possible solutions and its impact on Ethiopia are presented in the educational column. The reasons for job stress and the methods to control it, is also entertained in the same column. Finally, a short story and others are presented in the myscellany section.

We wish you a pleasant reading time!

የኢ.ብ.ባ. ሠራተኞች የሚተዳደሩበት ደንብ ይፋ ሆነ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በሚኒስትሮች ም/ቤት በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 24 መሠረት የባንኩ ሠራተኞች የሚተዳደሩበት ደንብ ይፋ ሆነ፡፡

ባንኩ በመንግሥት የልማት ድርጅቶችም ሆነ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ አዋጅ ውስጥ የታቀፈ ባለመሆኑ ምክንያት በባንኩ እና በሠራተኞቹ መካከል ያለው ግንኙነት የህግ ክፍተት ይታይበት እንደነበር እና ሠራተኛው ይተዳደር የነበረው በፍ/ቤት ውሳኔ በማህበር ተደራጅቶ ከባንኩ ጋር በአደረገው የህብረት ስምምነት መሠረት መሆኑን ተሻሽሎ በፀደቀው የባንኩ የማስፈጸሚያ አዋጅ ላይ ተገልጿል፡፡

ብሔራዊ ባንክ ካለው ተልዕኮና ኃላፊነት አኳያ በሲቪል ሰርቪስ አዋጅ 515/2000 መሠረት ለማስተዳደር ከመንግስት በጀት የማይደብለት በመሆኑ፤ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ለማስተዳደር ደግሞ ለንግድና ለትርፍ የተቋቋመ ባለመሆኑና ዋነኛ ተግባሩ የአገሪቱን የገንዘብ ተቋማት መቆጣጠር በመሆኑ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ልዩ ህግ እንዲተዳደር ረቂቅ ደንቡ መዘጋጀቱን የባንኩ ገዥ ክቡር አቶ ተክለወልድ አጥናፉ አብራርተዋል፡፡

የህብረት ስምምነቱ የተቀረፀው በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ቢሆንም፤ በተሻሻለው አዋጅ ውስጥ የሠራተኛውንና የባንኩን ግንኙነት በግልጽ የሚያስቀምጥ ደንብ በሚኒስትሮች ም/ቤት እንደሚወጣ በተደነገገው መሠረት ረቂቅ ደንቡ ሊዘጋጅ እንደቻለ ተመልክቷል፡፡

በረቂቅ ደንቡ ላይ የባንኩ የበላይ አመራር ከሠራተኛው ጋር ህዳር 28/2001 ዓ.ም. ውይይት ባደረገበት ወቅት፤ ደንቡ የባንኩንና የሠራተኛውን ግንኙነት በግልፅ የሚያስቀምጥ ጤናማ የሆነ ግንኙነት እንዲጎለብት የሚያደርግና የሠራተኛውን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ አዳዲስና የተሻሻሉ ጉዳዮችን ያካተተ መሆኑን ክቡር ገዥው ገልፀዋል፡፡

በረቂቅ ደንቡ ላይ አንቀጽ በአንቀጽ ውይይት የተካሄደ ሲሆን፤ በዚህ ወቅት ግልጽ መሆን ያለባቸው፤ መሻሻል እና መካተት የሚገባቸው ሀሳቦች በሠራተኛው ተነሥተው ከክቡር ገዥው ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ደንቡ በሚኒስትሮች ም/ቤት ፀድቆ ከታኅሣሥ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በሥራ ላይ መዋሉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

Discussion held on the draft MFI Business Proclamation

The National Bank of Ethiopia (NBE) held a half day discussion on Dec.15/08 with the Ethiopian Microfinance Institutions (EMFI) on the new draft proclamation prepared by the Bank.

H.E.Ato Teklewold Atnafu, Governor of the National Bank of Ethiopia (NBE) after his welcoming speech said that, it is decisive and compulsory for the governing body to set a new regulation and updating the existing one inline with the dynamism of the sector.
The Bank arranged this discussion forum to enable EMFI, forward their views on the draft document and for its subsequent implementation, the Governor said. He also explained that, the Bank has looked in to national and international experiences to make the draft proclamation more profound. In this regard, foreclosure law, tax treatment of MFI, penalty on operation of MFI business without license, MFI liquidation process, purchase and sell of Gold and MFIs' upgrading to commercial banks are among those incorporated in the new proclamation.

Dr. Wolday Ameha, Director of AEMFI noted that the draft proclamation has treated all important issues and concerns of MFI, which is a great breakthrough. Various questions and opinions were raised by participants and replies were given by the Governor.

Including the Director of AEMFI, 22 heads of MFI were in attendance. The proclamation becomes effective after the endorsement by the House of Peoples' Representatives and issued on the Negaret Gazette. Currently, 30 MFI are operating through out the country.

Academy offered one month training

The Ethiopian Academy of Financial Studies (EAFS) under the auspices of the NBE, offered training on crime control, crime investigation, research, domestic banking operations policies and procedures, international banking practices, insurance principles and practices, NBE's directives on foreign exchange during November 24, 2008- January 21, 2009. The professionals were drawn from various departments of the Federal Ethics and Anti-Corruption Commission (FEACC).

Ato Mesfin G/Sellassie, Director of the Academy told Birritu about the importance of the training that, since the commission is engaged in tackling corruption and mal-practices in the country, it gives immense opportunities to the trainees to know key operational activities in banks and insurance companies and possible rooms that lead to corruption.

Among the participants, Ato Berhanu Abate, investigation team leader and Ato Zeleke Assefa, advisor in the Department of Corruption Protection, explained that the major activities of the Commission are educating and sensitizing the public about the effect of corruption, ways of tackling and at the same time undertake professional investigation. Hence, knowing the activities of the aforementioned institutions and likely treats they may face is vital while conducting anti-corruption studies and investigations. 27 trainees attended the training.

Determinants of International Tourism Flows to Ethiopia

By: Getachew Ahmed

1. Introduction

The World Tourism Organization (WTO) defines tourism as "*the activities of persons traveling to and staying in places outside their usual environment for not more than one consecutive year*". International tourists are "*tourists who stay at least one night in a country where they are not residents*". From now on when we talk about tourism we are talking about international tourism.

Worldwide, international tourism receipts are estimated at USD 680 billion in 2005. In absolute terms, international tourism receipts increased by USD 47 billion, an amount comparable to the receipts of the world's second biggest tourism earner, Spain, or to the combined receipts of the Caribbean, Central America, South America and South Asia (WTO,2006).

According to the same source, Africa performed best of all regions in 2005, with an increase in arrivals estimated at around 9% for the second consecutive year. Growth was about as strong in Sub-Saharan Africa (9%) as in North Africa (8%). Algeria reported 17% more arrivals, while Morocco increased arrivals by 7% and Tunisia by 6%. Among the Sub-Saharan destinations, particularly remarkable results were reported by the Democratic Republic of Congo (103%), Swaziland (83%), Gambia (23%) and Senegal (15%). Major destinations such as South Africa (10%), as well as the island destinations of Seychelles (7%) and Mauritius (6%), all improved on their 2004 results. Kenya also reported strong growth (23%).

The main factors boosting tourism demand for African destinations are product improvement and diversification. Investment in infrastructure has also been very positive, and enhanced cooperation between the public and private sectors has helped to ensure increased benefits for all stakeholders.

Although the importance of tourism in the Ethiopian economy is widely recognized, little attention has been given to explain systematically its determinants. Empirical studies in explaining the international demand of tourism in Ethiopia are limited. The economic dimensions of tourism to Ethiopia and specifically the determinants of the demand for Ethiopia as a tourist destination are neglected in the economic research literature.

The objective of this study is to estimate the long run relationship between the foreign exchange earnings from tourism and its determinants such as income of the tourist, relative prices (real effective exchange rate), war and/or political instability, drought and market liberalization in the destination.

2. Tourism in Ethiopia: An overview

Tourism brings obvious economic benefits, with the two most important being the generation of foreign exchange and the creation of jobs. Ethiopia is no special in this respect. As shown in the following figure, overall, tourism has grown by 12.5% and 17.9% for the last fifteen years in terms of the number of arrivals and the forex earnings from travel respectively. After mid 2002, both of these indicators surged scoring 17.3% and 37.3% growth rates. Despite its positive endowments and good growth in tourism over the past fifteen years, it remains true that Ethiopia's tourism potential is underutilized and underdeveloped.

Figure 2:: Tourism arrivals and forex earning over time (1988-2005)



Source: Ethiopian Tourism Commission

As the table below shows more than 31% of Ethiopia's tourism arrivals come from Africa. The other share of 26% of the total tourism arrivals come from Europe. America, Middle East and Asia contribute 15.4%, 12% and 6% respectively.

Figure 3: Share of Tourist Arrivals from Total



Source: Ethiopian Tourism Commission

3. Literature Review: The Demand Function of Tourism

According to the literature, the underlying theory that explains tourist flows between the origin and the destination country is based on the demand function. The product resulting from the demand of tourism is an aggregate amount of the individuals' desire to travel within a specific time period and following this is the foreign exchange earning flowing from travel services given to the tourists.

Classical economic theory implies that the major determinants of the demand for foreign tourism should include: the price of tourist goods and services relative to the price of relevant substitutes, the incomes of tourists and any other specific factors which may alter the tastes of travelers for tourism (Walsh, 1996). Following this theory and the majority of empirical studies, the flows of tourism between the receiving and the supplying countries can be specified by using the demand function of the type:

$$Q_t = f\,(Y_t, P_t)$$

where Q stands for tourist consumption of tourism services in the receiving country, Y is income per capita of the supplying country (country of origin of the tourist) as a measure of its purchasing power capacity, and P is a relative price index to measure price levels between the origin and the destination countries.

The income of the importer country is the primary factor that affects tourism demand. In fact, the larger the purchasing power of the countries potential demanders, the more likely it is that their citizens can afford to purchase a good or service from abroad, all other things being equal. The second important determinant of the demand, in the model, for tourism is relative price between the receiving and the sending countries. Price depends not only on the price of the good in the origin country but also on the exchange rate.

In developed countries, the determinants of tourism are income, price, exchange rate between the currencies of the destination and origin country, transportation costs, and population (Naudé and Saayman:2004). Naudé and Saayman reported that the traditional determinants of the so called "developed countries" determinants such as income, price and cost of travel are not significant in explaining the demand for tourism in developing countries as a tourism destination. Rather political stability, marketing and information, drought, tourism infrastructure, the level of development in the destination are key determinants of tourism flow to these countries. There is a wide variety of models in the tourism literature for estimating tourism demand and forecasting some measures of tourism consumption in the destination country. Advanced econometric techniques have recently been applied.

4. Specification of the Model

4.1 Variables of the Model: Tourism is a sector that involves a multiplicity of economic activities responding to differentiated demands with specific characteristics at the national and international levels. The complexity and interaction of the tourism activities justify its consideration as a special sector that integrates a set of economic activities related mainly to traveling and accommodation services. The combination of demand (travel decision) and supply (accommodation provision) characteristics at the national and international levels creates some difficulties in modeling the tourism activity as a whole. However, the increasing importance of the tourism sector in terms of its contribution to the national product, employment and the balance of payments creates the need to investigate the determinants of tourism flows within a specific country, and especially for countries having abundant potential of the tourism industry. This study models the foreign demand for tourist services in Ethiopia in the same way as the demand for any other good or service from abroad.

$$TR_t=f(PY_{t,}RR_{t,}DD_{t,}DW_{t,}DM)$$

Where PY_t is the the per capita income of the countries in the sample, RR_t is the real effective exchange rate. DD_t, DW_t and DM_t are dummies capturing drought , war and/or political instability and market liberalization respectively.

Dependent Variable**:** The dependent variable in this study is the foreign exchange generated by this sector. However, the variable selected as proxy for the dependent variable has some limitations and the following three points should be noted. First, this variable includes all foreign exchange generated by all types of tourists (business and recreation) and does not allow us to distinguish the impact of changes in the explanatory variables on each type of traveler. Secondly, the data doesn't allow us to separately see tourism demand from each country of origin. Lastly, it is assumed that the receipts from tourist arrivals of eleven countries which account about 70% of the total tourist arrivals determine the movement in the changes of the total earnings from travel.

Independent Variables**:** We use real per capita income of the sending country (which also captures the population factor) defined by the following ratio:

$$Y_{i,t} = NGDP_{i,t/}GDP\ deflator_{i,t}.POP_{i,t}\ ,$$

Where, NGDP is Gross Domestic Product at current market prices, GDP deflator is proxy for price level to change nominal GDP to real GDP and POP is Population.

Another determinant of the demand for tourism is relative price between the receiving and the sending countries. It is not just the prices in the destination country which are important but also, relative price differences between the destination and the generating country. If prices in destination countries increase by more than those of the generating country and, this is not (fully) compensated for by changes in exchange rates then, the relative cost of travel abroad has clearly risen. For the purpose of this study real

effective exchange rate (REER) is used to capture the influence of relative prices where increase in REER indicates appreciation and decrease depreciation of the real effective exchange rate. Moreover, dummy war (DW), dummy drought (DD) and dummy market (DM) which are expected to be relevant for the Ethiopian case are included in the model.

The tourism demand function is estimated in log-log form so that the estimated coefficients can be interpreted as elasticities. The basic framework for the tourism demand function is as follows:

$$lnTR= \beta_0+\beta_1 \ln PY+\beta_2 lnRR+\beta_3 DD +\beta_4 DW + \beta_5 DM+ \Sigma$$

Where TR is foreign exchange earning generated from travel, PY is the per capita income of countries in the sample, RR real effective exchange rate, DW is the dummy for war and /or political instability, DD is the dummy for drought/famine, DM is the dummy variable used to capture liberalization.

The expected signs for the above variables are positive for per capita income (PY) and dummy market (DM) where as negative for real effective exchange rate (RR), dummy variables of war and/or political instability (DW) and drought (DD).

4.2. The Nature and Sources of Data

The paper applies annual data of 34 years (from 1973 to 2006). The paper analyses the determinant of Ethiopian tourism based on the data of selected samples of eleven countries (France, Germany, India, Italy, Japan, Kenya, Netherlands, Saudi Arbia Switzerland, UK and USA) which constitute more than 65% of the total tourist arrivals. The data source on the arrivals of tourists by origin is Ethiopian Tourism Commission.

Total travel earnings are taken as a dependent variable (TR) as there is no foreign exchange earning by country of origin. The source of this data is the National Bank of Ethiopia (NBE), ERMPD data base. Data on per capita income of countries calculated in such a way that the nominal GDP is divided by the GDP deflator and then by their population to get the per capita income of each country. The sum of the per capita income of these countries is taken as explanatory variable (PY). The source of these input data is International Financial Statistics (IFS). Real Effective Exchange Rate is defined as the currencies of the respective countries per birr which in effect imply appreciation of the currency is an increase in the magnitudes of REER. The data source for this variable is National Bank of Ethiopia (NBE), ERMPD data base.

4.3. Time Series Properties of the Data

To estimate the long-run relationship of the variables of the model for the period 1973-2006, we tested the behaviors of the variables over the time mentioned. The unit root characteristics of the data are examined. To examine the uni-variate time–series of the data, Augmented Dickey-Fuller (ADF) unit root tests are carried out on the series. Table 1 shows that the ADF tests statistics for all of the variables are stationary in their first differences [$I_{(1)}$].

Table 1: Results of the unit root tests on time series of tourism arrivals, per capita income and real effective exchange rate.

Variables	Constant		Trend and	
	Level	First diff.	Level	First diff.
lnTR	0.316232	-3.374779**	-3.763609**	-3.44534***
lnPY	-0.969946	-4.195318*	-3.298301***	-4.168817**
nRR	-1.529194	-4.343404*	-2.556102	-4.354794*

The stars *, ** and *** indicate rejection of the null hypothesis of a unit root at 1, 5 and 10 percent significance levels.

According to the ADF tests compared with the appropriate critical values in Table 1, the null hypothesis of the unit root (no long run relationship between forex earning, per capita income and real effective exchange rate) is rejected in favor of the alternative hypothesis. This means that the variables included in the models are co-integrated. That is we can rely on our long-run estimated parameters since we don't have the problem of spurious regression.

1. Estimation of Elasticities and Interpretation of Results

The coefficients of those explanatory variables specified in logarithmic form may be interpreted as elasticities. As can be seen, some dummy variables which were included in the hypothesis as outlined above have not been included at this stage because they are found insignificant.

Long-run

LnTR= $\beta_0 + \beta_1 lnPY + \beta_2 lnRR$

LnTR= -18.69 + 3.02lnPY - 0.86lnRR

St. Error (3.556) (0.433) (0.305)

T-stat: -5.256 6.982 -2.799

P-value (t-stat): (0.000) (0.000) (0.0087)

Adjusted R-squared: 0.8226 F-stat: 77.5451 [0.0000]

Heteroscedasticity Test: White's stat=2.2569 [0.0762]

Normality Test: Jarque-Bera= 0.7656 [0.6819]

Consistent with previous studies on tourism demand, per capita income in our major trading partner countries are positively related to the demand of tourism. As per capita income increases, demand for tourism also increases, with elasticity greater than one. Moreover, these countries appear much more sensitive to changes in their real per capita income levels (i.e. with an income elasticity value of 3.02) than to real effective exchange rate movements in the long run (with price elasticity of 0.86) in the long run.

Short-run dynamics

Using the information provided by the unit root test of the error term of the long run estimates, an Error Correction Model (ECM) is constructed to obtain the short-run elasticities. Modeling the short-run dynamics will provide information concerning how adjustments are taking place among the variables, to restore long-run equilibrium , in response to short-term disturbances in the demand for tourism in Ethiopia.

d(lnTR)= $\beta_0 + \beta_1 d(lnPY) + DW + ECM(-1)$

d(lnTR)= 0.091+1.01d(lnPY)- 0.23DW-0.26ECM(-1)

St. Error: (0.0422) (0.4823) (0.0967) (0.0911)

T-stat: 2.164 2.102 -2.343 -2.881

P-value (t-stat) :(0.039) (0.044) (0.026) (0.007)

Adjusted R-squared: 0.310804 F-stat: 5.8103[0.00308]

Heteroscedasticity Test: White's stat=2.2569 [0.0762]

*Obs*R-Squared=9.7667 [0.0821]*

Normality Test: Jarque-Bera= 0.7656 [0.6819]

In the short run as expected, per capita income is positively related to tourism demand. A 1.0 percent increase in the major trading partners' income per capita raises tourism demand (earning from travel) by about 1.0 percent (unitary elasticity). As we saw in the long run regression results, relative prices (real effective exchange rate) were negatively associated with tourism demand. In the short run, there is no significant relationship between price and the demand for tourism. This absence of relationships between demand for tourism and relative price in the short run may have come from the nature of the data on the latter. Firstly, the use of the REER index as a proxy for relative prices may distort results, given that it does not truly capture relative tourism prices – a hotel price index would have been preferred. It may be argued

these hotel prices are included in the CPI, but these prices might not have big weights in the calculation of the CPI. It they were given greater weights in the calculation, and then the CPI would appropriately show the movements in the hotel prices. The model also does not take into account transportation costs, such as airfares, and substitution prices. These omitted variables could have had a significant influence on the model. Unsurprisingly, years of wars and/or political instability deters somewhat tourism demand in the short run.

The ECM term is significant and the negative coefficient guarantees that the series is not explosive and that in the long-run, convergence is achieved. The coefficient of this term implies that a deviation from long-run tourism demand in one period is corrected by around 26.2 percent in the next.

6. Concluding Remarks

The purpose of this study is to gain insight into the Ethiopian tourism industry and to estimate the long run relationship and short-run dynamics between the foreign exchange earning from tourism and its determinants such as income of the tourist, relative prices, war and/or political instability, drought and market liberalization in the destination.

Tourism is clearly an important industry for Ethiopia, being the major foreign exchange earner for the country. Co-integration and error correction techniques followed by ordinary least squares were used to construct a tourism demand model for Ethiopia. In the long-run, the results suggest that income in our major trading partner countries are positively related to the demand for tourism, with a long-run elasticity of around 3.02 percent. As expected, an increase in relative prices decreases tourism demand. But in the short run, while income per capita income is positively related to tourism demand, relative prices were found to have an insignificant relationship between price and the demand for tourism. Years of wars and/or political instability have been found to deter tourism demand in the short run.

7. Recommendation

a. The first suggestion is to make future research especially in the areas of tourism demand models as a means to greater understanding of the industry. Demand models should explicitly attempt to include developing nations to complement past knowledge about what drives tourism growth to the most vulnerable destinations. More advanced statistical measures than those used here should be employed, to more accurately capture the nature of any effect, and what sources contribute to that effect. Finally, the above relationships should be examined in more detail on the scale of individual countries, to see which areas are most prone to the demand and volatility in the industry.
b. Secondly, all policy initiatives must be directed to stimulating total foreign exchange earnings from tourists and more specifically, to attempt to boost average expenditure per capita. Emphasis should be given in accelerating overseas visitor per capita expenditures particularly in origins such as the US, UK, France, Italy, Saudi Arabia, Kenya, India, Japan, Netherlands and Switzerland which contribute much more to revenue than to numbers. National expenditure in terms of, for example advertisement, should be directed accordingly.
c. Finally, as regards the supply conditions, the most favorable condition should be created in terms of the number of standard hotels, airports etc. The more rooms, the higher the capacity, and therefore the more competitive the country's tourism sector. For instance, a certain volume of hotel rooms may be necessary to convince airlines to establish routes as well as for justifying investment in complementary infrastructure such as roads. Similarly, tourism marketing is also important to capture the networks of tourist flows.

References

1. A. Khalik Salman, Estimating Tourist Demand Through Cointegration Analysis:Swedish Data, Social Sciences Department, Mid Swedish University,Sweden.
2. Daniel J. Stynes, Approaches to Estimating the Economic Impacts of Tourism; Some Examples, 1999.
3. Joaquín Alegre ,Llorenç Pou: AN ANALYSIS OF THE MICROECONOMIC DETERMINANTS OF TRAVEL FREQUENCY, Department of Applied Economics Universitat de les Illes Balears.
4. Mary Walsh, Demand Analysis in Irish Tourism, University of Limerick, Journal of the Statistical and Social Inquiry Society of Ireland Vol.XXVII, Part IV.
5. Resina Katafono, Aruna Gounder: Modeling Tourism Demand in Fiji, Working Paper 2004/01, Economics Department, Reserve Bank of Jiji, Suva, Fiji.
6. Tihomir Stu~ka : A Comparison of Two Econometric Models (OLS and SUR) for Forecasting Croatian Tourism Arrivals , Croatian National Bank. Working Papers July 2002
7. UNWTO: World Tourism Barometer, World Tourism Organization Volume III, No. I, January 2005.
8. W.A. Naudé & A. Saayman, The Determinants of Tourist Arrivals in Africa: A Panel Data Regression Analysis, Paper prepared for the International Conference, Centre for the Study of African Economies, St. Catherine's College, University of Oxford, 21 – 22 March 2004.

የአሜሪካ የፋይናንስ ሥርዓት ቀውስ መንስዔዎች የመፍትሔ ሃሳቦችና በኢትዮጵያ ላይ የሚኖረው እንድምታ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

1. መግቢያ

1. የአሁኑ የአሜሪካ የፋይናንስ ሥርዓት ቀውስ ከጀመረ ብዙ ዓመታት ሆኖታል ብለው የሚከራከሩ የፋይናንስ ኤክስፐርቶች ያሉ ቢሆንም፣ የችግሩ ግልፅ ምልክቶች መታየት የጀመሩት ግን እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በጁን 2007 ገደማ ነው፡፡ በዚህ ወቅት አካባቢ ቤር ስተርንስ (Bear Stearns) የሚባል ትልቅ የአሜሪካ የኢንቬስትመንት ባንክ ከቤት ልማት (real estate/mortgage) ጋር የተያያዙ በርካታ የብድር ሰነዶች ስለገዛና የቤት ልማት የኢኮኖሚ ዘርፍ እያቆለቆለ በመምጣቱ የመክሰር ምልክቶች አሳዬ፡፡ በተጨማሪም፣ በእንግሊዝ ሀገር ኖርዘርን ሮክ (Northern Rock) የሚባለው የሞርጌጅ ባንክ ከሥሮ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ዋለ፡፡ በካፒታሊስት ሀገር በግል ካፒታል የተቋቋመ ባንክ በመንግሥት የመወረሱ ጉዳይ እንደ አስገራሚ ክስተት ተቆጥሮ በዓለም መገናኛ ብዙኃን ከፍተኛ የመነጋገሪያ አርእስት ሆኖ ሰነበተ። ከቤት ልማት የብድር ሰነዶች ጋር የተቆራኙ የጀርመን ባንኮችም ከፍተኛ ችግር ውስጥ ገብተዋል፤ ከእነዚህም ውስጥ IKB Deutsche Industriebank እና Bavaria State Bank ይገኙበታል፡፡ በአሜሪካ በተከተታይ Citigroup, Merill Lynch, Jpmorgan Chase, Indymac, Fannie Mae and Freddie Mac, Lehman Brothers, AIG Washington Mutual, እና የመሳሰሉት ባንኮች እና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ለኪሣራ አደጋ የተጋለጡ መሆናቸው ተረጋግጦ፤ ከፊሎች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ዋሉ፤ ከፊሎቹ ደግሞ በይፋ መክሰራቸው ተገለፀ፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለም ቀውሱ በዓለም አካባቢ እየተስፋፋ የመጣ ቢሆንም፣ በበለፀጉ ሀገሮች ያሉት የፋይናንስ ገበያዎች አሠራር እጅግ የተራቀቀና የተወሳሰበ በመሆኑ የቀውሱን መንስዔዎች በትክክል ለመጠቆምና የመፍትሔ ሃሣቦችን ለማቅረብ የበርካታ የፋይናንስና የምጣኔ ሐብት ባለሙያዎችን ብቃት ተፈታትኗል፡፡

2. በበለጸጉ ሀገሮች ያሉትን የፋይናንስ ገበያዎች ውስብስብ የሚያደርገው በዋናነት የብድር ሰነዶች የተጠላለፈ ግብይት (securitization) ሥርዓት ነው፡፡ የወለድና የዋና ካፒታል ክፍያዎች የሚደረግባቸው የብድር ሰነዶች ራሳቸው መያዣ እየሆኑ ሌሎች የዕዳ ሰነዶችን ይፈጥራሉ፡፡ እነዚህም እንደዚሁ በተራቸው ሌሎች የዕዳ ሰነዶችን እጅግ በተወሳሰበና በተጠላለፈ መንገድ እየወለዱና እየተዋለዱ የድንበር-ዘለል ካፒታል መሸጋገሪያና መተላለፊያ በመሆናቸው የዓለም የፋይናንስ ገበያዎችን የተቆላለፉ ያደርጓቸዋል፡፡ ለዚህም ነው በአሜሪካ የደረሰው የፋይናንስ ሥርዓት ቀውስ በዓለም ዙሪያ ሊያስተጋባ የቻለው፡፡

3. አቢይ የቀውሱ ገፅታ በተለይ የቤት ብድር የወሰዱ ተበዳሪዎች ብድሩን መመለስ በስፋት ማቆማቸው ነው፡፡ በተለይ ከደረጃ በታች (sub-prime) ተብለው የሚመደቡት የቤት ብድር ክፍያዎች በከፍተኛ መጠን ተቋረጡ፡፡ ችግሩ ደረጃቸውን ወደ ጠበቁት (prime) የቤት ብድር ተጠቃሚዎችም የተዛመተ ሲሆን፤ አሁን ደግሞ ለመኪና ብድር የወሰዱ ግለሰቦች የብድር ክፍያዎችን እያቋረጡ እንዳደሆነ ይነገራል፡፡ ቀደም ብሎ ጀምሮ የነበረው የአጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መቀዝቀዝ እየተባባሰ መጥቶ፤ ያለማቋረጥ ያሻቅብ የነበረው የቤት ዋጋ በከፍተኛ መጠን ቀነሰ፡፡

4. በአጠቃላይ በኢኮኖሚው ውስጥ ባሉት የተለያዩ ተዋንያን መካከል አለመተማመን በመስፈኑ፤ በባንኮች መካከል የነበረው እርስ በእርስ የመበዳደር ሥርዓት ክፉኛ ተዳከመ፣ በብድር እጥረት ምክንያት የሥራ ማስኬጃ ጥሬ ገንዘብ እጥረትም በመፈጠሩ የባንክ የሥራ እንቅስቃሴ በእጅጉ ቀዘቀዘ። በፋይናንስ ዘርፉ የደረሰው ቀውስ የአጠቃላይ ኢኮኖሚውን እንቅስቃሴ ይበልጥ እያባባሰው ስለመጣ፣ የተለያዩ ኩባንያዎች በሙሉ አቅማቸው ለመንቀሳቀስ አልቻሉም። አዲስ ኢንቬስትመንትም እየቀነሰ በመምጣቱ የዕቃና የአገልግሎት ሽያጭ በከፍተኛ ደረጃ ከማሽቆልቆሉ በተጨማሪ ሥራ አጥነት ተንሰራፍቶ አጠቃላይ የኢኮኖሚ መቀዝቀዝ እውን ሆነ። ይህ በአሜሪካ ጉልቶ የተከሰተው የፋይናንስ ሥርዓት ቀውስ በአውሮፓ፣ በእስያ፣ በላቲን አሜሪካ፣ በአውስትራሊያና በሌሎችም አካባቢዎች ጉዳ ተፅዕኖውን ማሳደር ጀመረ።

2. የፋይናንስ ሥርዓቱ ቀውስ አበይት መንስዔዎች

5. የቀውሱ መንስዔዎች በአብዛኛው ከአበዳሪዎች በኩል የመነጩ ናቸው ቢባልም፣ ተበዳሪዎችም በመጠኑም ቢሆን ለቀውሱ አንድ መንስዔ እንደሆኑ ተረጋግጧል። ዋና ዋናዎቹ አበዳሪዎች ራሳቸውም ተበዳሪዎች ስለሆኑ የእነዚህ ሚና በጣም የጐላ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይሆንም። የፋይናንስ ድርጅቶች በተለይም መደበኛ ባንኮች፣ የኢንቬስትመንት ባንኮችና የኢንሹራንስ ድርጅቶች በተወሳሰበና በተደበላለቀ (securitization) ሁኔታ የብድርና ዋስትና አገልግሎቶቹን ለተጠቃሚው ሕዝብ ከመስጠታቸው በተጨማሪ እርስ በራሳቸውም ይበዳደራሉ፤ ዋስትናም ይሰጣጣሉ። ይህን የተጠላለፈ የማበደርና የመበዳደር መረብ ፈታትቶ ግልጽ በሆነ መንገድ ለማሳየት አዳጋች ቢሆንም፣ ዋናዎቹን የአበዳሪና የተበዳሪ የግንኙነት መስመሮች ለይቶ በማውጣት ሁኔታውን ይበልጥ ለመገንዘብ ይቻላል።

6. በመጀመሪያ ድርጅታዊ አበዳሪዎች የተራቀቁ፣ የተወሳሰቡና የተጠላለፉ የብድር ሰነድ ዓይነቶችን በብዛት ማውጣት (securitization)ጀመሩ። በእነዚህም ሰነዶች አማካይነት ብድር ብድርን እየወለደ ከመጠን በላይ እያደገ እንዲሄድ አደረጉ። የብድር ሰነዶች የተወሳሰቡ ከመሆናቸው የተነሳ የፋይናንስ ዘርፍ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኖች ራሳቸው በሚገባ ሊረዷቸውና ተገቢውን ቁጥጥር ሊያደርጉባቸው አልቻሉም። በመሆኑም፣ በመደበኛ ሂሣብ ውስጥ መያዝ ያለባቸው ሀብቶችና ዕዳዎች ከመደበኛው ሂሣብ ውጪ (off balance sheet) ሲመዘገቡ፣ ተቆጣጣሪዎች ይህንን ተመልክተው ኣላስቆሙም። በተጨማሪም ደረጃ መዳቢዎች (rating agencies) ድርጅቶች ከጥቅም ግጭት የተነሣ ከእንከን ነፃ የሆነ ሥራ መሥራት እንዳልቻሉ ተረጋግጧል። እንደሚታወቀው እነዚህ ድርጅቶች ለሚሠጧቸው አገልግሎቶች የሚከፍሏቸው መደበኛ ባንኮች፣ ኢንቨስትመንት ባንኮችና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ራሳቸው ናቸው።

7. ሁለተኛ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን የቤት ዋጋ በከፍተኛ መጠን እየጨመረ መሔድ ለቤት ግዥ ወይም መሥሪያ የሚበደሩ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን የመበደር አቅም በከፍተኛ ደረጃ መጨመሩ እንደ አንድ ምክንያት ይጠቀሳል። ለምሳሌ አንድ ግለሰብ ቤት ለመግዛት 50,000 ብር ያስፈልገዋል እንበል፤ 50,000 ብሩን ይበደራል፣ የገዛውን ቤት መያዣ ያደርጋል። በመካከል የቤቱ ዋጋ ወደ 100,000 ብር ከፍ ቢል፣ ተበዳሪው ከአበዳሪው ባንክ 50,000 ብር በተጨማሪ ሊበደር ይችላል፤ ጠቅላላ ብድሩ 100,000 ብር ይሆንና ወለድና የዋና ክፍያ በዚሁ የብድር መጠን ላይ በየጊዜው ይከፍላል። ተበዳሪው በተጨማሪ ብድር መልክ ያገኘውን 50,000 ብር ጥሬ ገንዘብ ለፈለገው ጉዳይ ሊያውለው ይችላል። ነገር ግን ይህ ዕዳ ተበዳሪው ከሚያገኘው ገቢ ላይ በወለድና በዋና ዕዳ ክፍያ መልክ ተቀናሽ መሆኑ የማይቀር ነው። ችግሩ ጉልቶ የተከሰተው የቤቱ ዋጋ በተፈጠረው ችግር ምክንያት በከፍተኛ ደረጃ ለምሳሌ ወደ 50,000 ብር መልሶ ሲወርድ

ነው። ያን ጊዜ ተበዳሪው ብድሩን ከመክፈል መቆጠብ ይጀምራል፤ አበዳሪውም በመያዣነት የያዘውን ቤት ቢወስድለት ይመርጣል። እዚህ ላይ፣ ዋናው ችግር ተበዳሪው የቤት ዋጋ ይጨምራል በሚል ግምት የተበደረውን ገንዘብ ገቢ ለማያስገኝ ጉዳይ ወጪ ማድረጉ፣ አበዳሪዎች ደግሞ መክፈል እንደማይችሉ ለሚገመቱ (sub-prime) ተበዳሪዎች ሁሉ በመደዳ ማበደራቸው እንደ ዋነኛ ምክንያት ይቆጠራል።

8. በአጠቃላይ ለተከሰተው ዓላምአቀፋዊ የፋይናንስ ቀውስ የሚከተሉት ምክንያቶች በዋናነት ይጠቀሳሉ።

ሀ. አበዳሪዎች ከሀገር ውስጥ ገንዘብ አስቀማጮችና እንዲሁም ከዓለምአቀፍ ምንጮች (በተለይም ከነዳጅ አምራች ሀገሮችና እንደ ቻይና ካሉ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ካላቸው ሀገሮች) ያሰባሰቡትን ከፍተኛ የገንዘብ ክምችት በስፋት ለማበደርና እርስ በርስም ለመበዳደር ሲሉ በጣም በርካታና የተወሳሰቡ የብድርና የዕዳ ሰነዶችን ፈጥረው በነዚህም አማካይነት ከፍተኛ የብድር መጠን ማሰራጨታቸው፣

ለ. የቤት ዋጋ ይጨምራል እንጂ አይቀንስም በሚል የተሳሳተ ግምት የመክፈል አቅማቸው አጠራጣሪ ለሆኑ ተበዳሪዎች ጭምር የቤት ብድር በስፋት መስጠቱ፤

ሐ. ብድር የመክፈል አቅም በጥልቀት ሳይገመገም ብድር የመስጠት አዝማሚያ እየጐላ መምጣት (sub-prime rate system)፣

መ. የሥራ ጥራት ደረጃ መዳቢዎች (rating agencies) ሥራቸውን በትክክል ለመሥራት አለመቻል፤

ሠ. በቤት ተበዳሪዎችና የብድር ደላሎች ዘንድ የማጭበርበር ድርጊቶች መፈፀማቸው፣

ረ. የፋይናንስ ዘርፍ ቁጥጥርና ክትትል መላላት፣

ሰ. ለአጠራጣሪ የብድር ሰነዶች ተገቢ ያልሆነ ዋስትና መስጠት፣

ሸ. የማዕከላዊ ባንኮች የገንዘብ ፖሊሲ መላላት፣ ወዘተ.

3. በበለጸጉት አገሮች የተከሰተውን ቀውስ ለመግታት የሚያስችሉ የመፍትሔ ሃሣቦች

3.1 የአጭር ጊዜ መፍትሄዎች

9. በአሜሪካ የጀመረው የፋይናንስ ሥርዓት ቀውስ ወደ አውሮፓና እስያ ሀገራት ተዛምቶ፤ በአጠቃላይ ዓለምአቀፋዊ ቅርፅ ይዟል። ከላይ እንደተመለከተው፣ የቀውሱ መንስዔዎች የተወሳሰቡ እንደመሆናቸው የሚያስከትሏቸው ተፅዕኖዎችም እንደዚሁ እርስ በእርሳቸው የተቆላለፉ ናቸው። ለዚህ ውስብስብ ዓለምአቀፋዊ ቀውስ መፍትሔ ለመፈለግ በዓለም ዙሪያ በርካታ ታዋቂ ኢኮኖሚስቶች፣ የፋይናንስ ጠበብቶችና ሌሎች ባለሙያዎች ሌት-ከቀን በመሥራት ላይ ናቸው። የአሜሪካ መንግሥትና ማዕከላዊ ባንክ በአጠቃላይ የአሜሪካ የኢኮኖሚ ቀውስ ሊያስከትል ከሚችለው ውድቀት ለመዳን የ700 ቢሊዮን ብር የዕርዳታ ፕሮግራም አዘጋጅተው ተግባራዊ በማድረግ ላይ ናቸው። የዚህ ፕሮግራም ውጤት ወደፊት የሚታይ ቢሆንም፣ የፋይናንስ ሥርዓቱ እንደገና እንዲንቀሳቀስ በማገዝ አጠቃላይ ኢኮኖሚውም እንዲያንሠራራ የሚረዳ መሆኑ ብዙዎች ይስማሙበታል። ሩሲያን ጨምሮ አንዳንድ የአውሮፓ ሀገሮች ተመሳሳይ እርምጃዎች ወስደዋል። በዋና ዋናዎቹ የለሙ ሀገሮች የሚገኙት ማዕከላዊ ባንኮች ለንግድ ባንኮችና ለሌሎች ባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች ብድር በመስጠት በጥሬ ገንዘብ (liquidity) እጥረት

ምክንያት የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት እየጣሩ ናቸው፡፡

10. ይህ አጠቃላይና ጊዜያዊ መፍትሔ ያነጣጠረው በቀውሱ መሠረታዊ ችግሮች ላይ ሳይሆን የተፈጠረውን የጥሬ ገንዘብ እጥረት በማቃለል የፋይናንስ ድርጅቶች የተለመደ እንቅስቃሴያቸውን እንዲቀጥሉና በፋይናንስ ድርጅቶች መካከል እንዲሁም በአጠቃላይ በተገልጋዩ ሕዝብ ዘንድ እየተሸረሸረ የመጣውን አመኔታ (confidence) እንደገና ለመመለስ ነው፡፡ በበለጸጉ አገራት መንግሥትና ማዕከላዊ ባንኮች የተወሰደው እርምጃም የሚከተሉት በጐ ውጤቶች እንደሚኖሩት ይጠበቃል፡፡

- በተለይ እስከተወሰነ መጠን ድረስ በባንክ ገንዘብ ያስቀመጡ ሰዎች የፈለጉትን ያህል ገንዘብ ማውጣት ይችላሉ፤ ይህም በአስቀማጮች ዘንድ አመኔታን ለመፍጠር ያግዛል፣

- መክፈል የሚችሉ ተበዳሪዎች አስፈላጊው የዕዳ ሽግሽግ እየተደረገላቸው የወሰዱትን ብድር እንዲከፍሉ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፣

- የፋይናንስ ድርጅቶች ለተበዳሪዎችና የኢንሹራንስ ፖሊሲ ለሚገዙ ደንበኞች የመክፈል አቅማቸውን በጥብቅ እየመረመሩ ብድርና ዋስትና እንደገና መስጠት ይጀምራሉ፣

- በፋይናንስ ድርጅቶች መካከል ከሞላ-ጐደል ተቋርጦ የነበረው የመበዳደር ሥርዓት እንደገና እንዲያንሠራራ ያግዛል፣

- የፋይናንስ ድርጅቶች የካፒታልና የመጠባበቂያ ገንዘባቸውን ለመገንባት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፣

- የፋይናንስ ድርጅቶች በተረጋጋ መንፈስ የሀብትና የዕዳ ሂሣቦቻቸውን እንዲያስተካክሉ ያግዛል፡፡

3.2 ዘላቂ መፍትሄዎች

11. ከላይ ለመግለጽ የተሞከረውን የተቆላለፈ ችግር ከመሠረቱ ለማቃለል ግን በርካታ ሌሎች ተዛማጅ እርምጃዎች ሊወሰዱ እንደሚገባ የፋይናንስ ጠበብቶች ይመክራሉ፡፡ ከሚሰጡት ዘላቂ መፍትሄዎች መካከል የሚከተሉት በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፡፡

- የተለያዩ የፋይናንስ ድርጅቶች የሚሠሯቸው ሥራዎች የሥራ ዳር ድንበር የሌላቸውና የተደበላለቁ እየሆኑ መምጣታቸው ለተከሰተው ችግር አንደኛው መንስዔ በመሆኑ፣ ቢያንስ በተወሰነ ደረጃ የፋይናንስ ድርጅቶች ቀድሞ እንደነበረው ሁኔታ የሥራ መስካቸው በተቻለ መጠን የተከለለ እንዲሆን ማድረግ፣

- የፋይናንስ ዘርፉን እንቅስቃሴዎች የመቆጣጠር ተግባር እንዲጠናከር በማድረግ አሁን ያለውን የላላ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት በተሻለ ዘዴ መተካት፣

- ከሀብትና ዕዳ ሂሣብ ውጪ (off balance sheet) የሚያዙ ሂሣቦች በሚገባ ተመርምረው በዋናው ሂሣብ ውስጥ መመዝገብ የሚገባቸው ሁሉ እንዲመዘገቡ ማድረግ፣

- የክስረት አደጋን ማከፋፈል በሚል ዘይቤ (risk distribution) እንደ እንጉዳይ የፈሉትን የብድር ዕዳ ሰነዶች (securitization) ምንነት በሚገባ ተረድቶ አደገኛ የሆኑት እንዲወገዱ ማድረግ፣ እና አገልግሎት በመስጠት ላይ ባሉ ሰነዶችም ላይ ጠበቅ ያለ ቁጥጥር ማድረግ፣

- ደረጃ መዳቢ ተቋሞች (rating agencies) ተግባራቸው ከጥቅም ግጭት ነፃ እንዲሆን በማድረግና አስፈላጊውን ቁጥጥር በማድረግ የሥራ ጥራታቸውን ማሻሻል፣

- በፋይናንስ ዘርፉ ውስጥ ሕገ-ወጥ ተግባራትን የሚፈፅሙ ግለሰቦችና ድርጅቶች ላይ ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ፣

ማዕከላዊ ባንኮች የአጠቃላይ ዋጋ ንረትን ብቻ ሳይሆን የአክስዮኖችንና የሌሎች ሰነዶችን ዋጋ (asset prices) ጭምር የሚከታተሉበትን ዘዴ መቀየስና ተገቢውን የገንዘብ ፖሊሲ እርምጃዎች እንዲወስዱ ሥልጣን መስጠት፡፡

4. የፋይናንስ ሥርዓት ቀውሱ በኢትዮጵያ ላይ የሚኖረው እንድምታ

12. እንደሚታወቀው አሁን የተከሰተው የፋይናንስ ቀውስ ኢትዮጵያን ጨምሮ በአፍሪካ ላይ ያለው ተጽእኖ በጣም አናሳ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ለዚህም ከሚሰጡት ምክንያቶች አንዱ የአፍሪካ ባንኮች የሚሰጡትን ብድር በሙሉ በመደበኛ የሂሳብ መዝገብ (balance sheet) ስለሚመዘግቡ ሁኔታው ከቁጥጥር ውጭ አለመሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛ በተጠላለፈ ሰነድ (securitization) የተሰጠ ብድር አነስተኛ እንዲያውም በአንዳንድ አገሮች ጭራሹኑ አለመኖሩ ነው፡፡ ስለሆነም ከደቡብ አፍሪካ በስተቀር በካፒታል ፍሰት ምክንያት የሚመጣ የፋይናንስ ችግር በአፍሪካ፣ በተለይም ደግሞ ከሰሃራ በታች ባሉ አገሮች ላይ በጣም ውስን እንደሆነ የኢኮኖሚና የፋይናንስ ጠበብት ይስማሙበታል፡፡

13. ነገር ግን ይህ ዓለምአቀፋዊ የፋይናንስ ሥርዓት ቀውስ በኢትዮጵያ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ የለም ማለት አይደለም፡፡ ስለሆነም ቀውሱ የሚኖረውን ጫና ለመዳሰስ አገሪቱ ከቀረው ዓለም ጋር ያላትን የኢኮኖሚ ግንኙነት መስመሮች ማጤን ያስፈልጋል፣ እነዚህም የግንኙነት መስመሮች፣ የውጭ ንግድ፣ ብድር፣ እርዳታና ሐዋላ፣ እና የውጭ ኢንቬስትመንት ናቸው፡፡

14. የውጭ ንግድን በተመለከተ፣ የፋይናንስ ቀውሱ የሚያሳድረው ተፅዕኖ በወጪና በገቢ ንግድ ላይ ይሆናል፡፡ ቀውሱ በተለይ በለሙት ሀገሮች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መቀዛቀዝን እያስከተለ ስለሆነ ኢትዮጵያ ወደ ውጭ ምትልካቸው ሸቀጦች ዋጋ በዓለም ገበያ ላይ ዝቅ ሲል ከኤክስፖርት የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢም ሊቀንስ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል፣ ኢትዮጵያ ከውጭ ሀገር የምታስገባቸው ዕቃዎች ዋጋ /በተለይ ነዳጅ፣ ማዳበሪያ፣ ብረትና የብረት ውጤቶች/ በተፈጠረው የኢኮኖሚ መቀዝቀዝ ዋጋቸው እየቀነሰ ስለሆነ በወጪ ንግድ ገቢ በኩል የሚደርሰውን ጉዳት ሊያካክሰው እንደሚችል ይታመናል፡፡ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተከሰተው የነዳጅ ዋጋ መቀነስ እዚህ ላይ እንደ ዓይነተኛ ምሳሌ ሊወሰድ ይችላል፡፡

15. የውጭ ብድርና ዕርዳታን ስንመለከት፣ የለሙት ሀገሮች መንግሥታት የደረሰባቸውን የፋይናንስ ቀውስ ለማስተካከል ከበጀቶቻቸው ጭምር ገንዘብ እየመደቡ ስለሆነ፣ ለታዳጊ ሀገሮች የሚሰጡት ብድርና ዕርዳታ ሊቀንስ ይችላል የሚል ግምት አለ፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያ የውጭ ብድርና ዕርዳታ በብዛት የምታገኘው ከአውሮፓና ከአሜሪካ እንደመሆኑ መጠን በእነዚህ ሀገሮች የደረሰው ከፍተኛ የፋይናንስ ቀውስ የሚኖረው እንደምታ በግልፅ ባይታወቅም አሳሳቢ ነው፡፡

16. በተመሳሳይ፣ እውጭ ሀገር ያሉ ኢትዮጵያውያን ወደ ኢትዮጵያ የሚልኩት ሐዋላ ሊቀንስ ይችላል ተብሎ ይገመታል፡፡ በአሜሪካና በአውሮፓ የደረሰው የፋይናንስ ቀውስና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መቀዛቀዝ፣ በእነዚህ ሀገሮች ያለውን አጠቃላይ የሥራ አጥነት የሚያባብሰው ከሆነ ውጭ ሀገር ያሉ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው የሚልኩት ሐዋላ ሊቀንስ ይችላል፡፡ ይህም በሀገር ቤት የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ችግር ላይ ከመጣሉም በተጨማሪ በክፍያ ሚዛን ላይ የራሱ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

17. ዓለምአቀፋዊው የፋይናንስ ቀውስ ከውጭ ኢንቬስትመንት አኳያ ሲገመገም ቀውስ ከአጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መቀዝቀዝ ጋር ተጣመሮ የመጣ ችግር እንደመሆኑ የውጭ ኢንቬስተሮች የሚያደርጉት ኢንቬስትመንት ይቀንሳል የሚል ስጋት አለ፤

18. በአጠቃላይ የፋይናንስ ቀውሱ በተለይ በኢትዮጵያ ላይ ሊያደርሳቸው የሚችሉትን ተፅዕኖዎች ዘርዘር ባለ መልኩ ሲገመገሙ የሚከተሉት እንድምታዎች ይኖሩታል።

የወጪ ንግድ

ከቡና፣ ከቆዳ ውጤቶች፣ ከቅባት እህሎች፣ ከአበባና ከወርቅ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ በመጠኑ ሊቀንስ ይችላል፣

የአገልግሎት ንግድ

የዓለም ኢኮኖሚ በመቀዝቀዙ ምክንያት ኢትዮጵያ ከቱሪዝምና ከአየር ትራንስፖርት አገልግሎት የምታገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ ሊቀንስ እንደሚችል ይገመታል፣

የገቢ ንግድ

ለነዳጅ፣ ለማዳበሪያ፣ ለኢንዱስትሪ ጥሬዕቃዎችና ለሌሎች የገቢ ንግድ ዕቃዎች የሚከፈለው የውጭ ምንዛሪ በመጠኑም ቢሆን እንደሚቀንስ ይገመታል፣

የውጭ ብድር እርዳታ

ኢትዮጵያ ከውጭ ሀገር የምታገኘው ብድርና ዕርዳታ የተጠበቀውን ያህል ላይመጣ ይችላል፣

ከውጭ ሀገር የሚገኝ ሐዋላ

በበለጸጉት አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በብዛት የጉዳቱ ሰለባዎች ከሆኑ በሐዋላ መልክ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ሊቀንስ ይችላል፣

የውጭ ኢንቬስትመንት

ከገለጸጉት አገራት ካሉ ባንኮች ብድር በማግኘት በአገራችን ኢንቨስት የሚያደርጉ ባለሀብቶች ሊቀንሱ ይችላሉ፣

ከላይ የተዘረዘሩት ተፅዕኖዎች ድምር ውጤት በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ያለውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በተለይም የልማት ጥረቱን በመጠኑ ሊያቀዘቅዘው ይችላል።

6. ማጠቃለያ

በአሜሪካ ተቀስቅሶ በአውሮፓ፣ በእስያና በሌሎች ሀገሮች እየተዛመተ ያለው ዓለምአቀፋዊው የፋይናንስ ሥርዓት ቀውስ በኢትዮጵያ ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ በዋናነት ከወጪ ንግድ ምርቶች አገልግሎቶች፣ ከሐዋላ እንዲሁም ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት የሚገኝ የውጭ ምንዛሪ ዕድገት ላይ መጠነኛ ቅናሽ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ይገመታል። የውጭ ምንዛሪ እጥረቱ ደግሞ በሀገሪቱ የልማት እንቅስቃሴ ላይ የራሱ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል። በሌላ በኩል የተፈጠረው የፋይናንስ ቀውስ እና ከዛ በኋላ በተከሰተው በኢኮኖሚ ዕድገት መቀዝቀዝ ምክንያት አንዳንድ የገቢ ምርቶች ዋጋ /ነዳጅ፣ ማዳበሪያና ብረታ ብረት/ በከፍተኛ ደረጃ ሊቀንስ በመቻሉ ቀውስ በኢትዮጵያ ላይ የሚያሳድረው ተጽኖ በጣም አነስተኛ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።

ዋቢ ሰነዶች

1. M & C Business: Chronology of Current Affairs, Sept. 15, 2008

2. Wikipedia.

3. Time, Sept. 29, 2008.

4. Financial Times, various issues.

5. 24/7 Wall St. Com.

Please send your articles to the
Editorial Office of BIRRITU
P.O. Box: 5550, National Bank of Ethiopia
EMAIL: birritu@ethionet.et
Addis Ababa, Ethiopia

የሥራ ውዓረዮ መግስጩጪጋ ቁዓዓራካው

ከማርታ በለጠ (ኢ.ብባ)

መግቢያ

የሥራ ውጥረት ወይም 'Job Stress' በዓለማችን አሳሳቢ የጤናና የኢኮኖሚ ችግር እየሆነ ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ከሆነ በርካታ ሠራተኞች በየጊዜው በዚሁ ሳቢያ ከባድ የጤና መታወክ እየገጠማቸው ነው፡፡ በኢኮኖሚው ላይም ቀላል የማይባል ጉዳት እያደረሰ ይገኛል፡፡

ለምሳሌ በአውሮፖ ብቻ በየዓመቱ ከአጠቃላይ ብሔራዊ ምርት ውስጥ 10% የሚሆነው ከውጥረት ጋር ተያያዥ በሆኑ ምክንያቶች ይታጣል፡፡ ይኸውም ሠራተኞች ከሥራ ገበታ ላይ ውጥረት በሚፈጥረው ሕመም ሳቢያ በመቅረት፣ ሥራ በመልቀቅ፣ በመሠላቸት፣ በመጨነቅና፣ በድብርት ስሜት ውስጥ ሆነው ሲሠሩ በሚያስከትሉት ጥፋት ነው፡፡ በተጨማሪም በዚያው በአውሮፖ ውስጥ በተካሄደው ጥናት እንደሚያመለክተው አሰሪ ድርጅቶች በዚሁ ችግር ሳቢያ ለከፍተኛ ወጪዎች እየተዳረጉ ነው፡፡ ለሕግ ጉዳዮችና ለካሣ ክፍያ ለሕክምናና ለመሳሰሉት ወጪዎች ሁሉ ተጋላጭ ሆነዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ምርትና ገቢ እየቀነሱ መሆናቸውን ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡ (ሞህቲንግ 1989)

አፍሪካ ምንም እንኳን የችግሩ ተጠቂ ብትሆንም የሥራ ውጥረት ምን ያህል ጉዳት እንዳደረሰ በአህጉር ደረጃ በቂ ጥናት የተካሄደበት መረጃ በድረ ገጽ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በአፍሪካ ውስጥ ካሉ ሐገራት ብዙ ስለ ስራ ውጥረት ጥናቶች የተካሄደባት አገር ደቡብ አፍሪካ መሆኗን የድረ ገጽ መረጃ ይጠቁማል፡፡ ወደ አገራችን ስንመጣ ደግሞ በኢትዮጵያ የሥራ ውጥረት መኖሩ አይካድም፡፡ ምክንያቱም በዚህ ዘመን ማንኛውም የዓለም ክፍል በውድድር ውስጥ ነው ያለው፣ ውድድር ደግሞ የለውጥ መሠረት ነው፣ ማንኛውም ለውጥ ደግሞ የአዎንታዊም ሆነ የአሉታዊ ውጥረት ምንጭ ነው፡፡ ይህንን ችግር ለመቆጣጠር የተካሄደ በቂ ጥረት ስለመደረጉ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡

የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ፡-

ስር የሰደደ የሥራ ውጥረትም ምርታማነትን ከሚቀንሱ ምክንያቶች እንደ አንዱ ስለሆነ አሰሪ ተቋማት ወይም ድርጅቶች ውስጣቸውን እንዲፈትሹና መፍትሄ እንዲሹ ለመጠቆም ያህል ሲሆን ሠራተኞችም ራሳቸውን እንዲያዩና እንዴት መቋቋም እንዳለባቸው እንዲረዱ ነው፡፡

በተጨማሪም በሥራ ውጥረት ዙሪያ ሰፋ ያለ ጥናት ለማጥናት ለሚፈልጉ ሁሉ እንደመነሻ ሃሳብ ለማገልገልም ጠቀሜታ አለው፡፡

የጽሑፉ ምንጭ

ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ሲሆን፤ ይህም ከተለያዩ የውጭ መጻህፍትና ድረ ገጾች ነው፡፡ የሐገራችንን ሁኔታ ከሚታየው እውነታ ጋር በተቻለ መጠን ለማዛመድ ተሞክሯል፡፡

የጽሑፉ ይዘት

I. ይሄ አጭር ፅሑፍ በሶስት ክፍሎች ተከፍሏል፡፡ የውጥረት ምንነትና ዓይነቱ የመጀመሪያው ሲሆን፤ ተከታዩ ክፍል በሥራ አካባቢ የሚፈጠር የሥራ ውጥረት ዓይነት፤ የሥራ ኃላፊዎችና የሠራተኞች የውጥረት መንስኤ ከነመፍትሄዎቻቸው፣ በተጨማሪም ማንኛውም ሰው ሊተገብረው የሚችል የሥራ ውጥረት መቀነሻ ቴክኒኮችንም አካቷል፡፡ በመጨረሻው ክፍል ውጥረት በጤና ላይ የሚፈጥረውን ችግር ካመላከተ በኃላ በማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሣብ በመዘርዘር ተቋጭቷል፡፡

II. የአእምሮ ውጥረት ወይም ውጥርት 'Stress' እና ዓይነቶቹ

1. የአእምሮ ውጥረት ወይም ውጥረት ስንል ምን ማለታችን ነው

ለንደን የሚገኘው የአእምሮ ውጥረት የመቋቋም ማዕከል የአእምሮ ውጥረት በcዎች ላይ ሊከሰት የሚችለው ሊቆጣጠሩት ከሚችሉት በላይ እንዲፈጽሙት የሚጠበቅባቸው ጉዳዮች ሲበዙ የአእምሮ መጨናነቅ ሲፈጠር ነው። ነገር ግን እነኚህ ሁኔታዎች በእያንዳንዱ ሰው ስብዕና፣ የአመለካከትና የግንዛቤ መጠን የውጥረቱም ልክ ይለያያል። በማለት 'Stress'ን አስቀምጠውታል።

1.1 የአእምሮ ውጥረት ወይም የውጥረት አጠቃላይ ሁኔታ

የውጥረት ዓብይ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ ለውጦች

1. አካባቢያዊ ሁኔታዎች
   - ያልተረጋጋ ኢኮኖሚ
   - ያልተረጋጋ ፖለቲካ
   - ፈጣን የቴክኖሎጂ ዕድገት
   - ማህበራዊ ሁኔታ
2. ሥራ አካባቢ የሚፈጠር የሥራ ውጥረት
   - ድርጅቱን ከመፍራት
   - ከሥራው የሚመነጭ
3. የግለሰቡ ሁኔታ
   - የቤተሰብ ችግር
   - የኢኮኖሚ ችግር
   - የግለሰቡ ማንነት

የግለሰቡ ስብዕና

- ነገሮችን የሚያይበት ሁኔታ አመለካከቱ
- የማህበራዊ ድጋፍ መጠን
- ከሁኔታዎች ጋር ያለው የመላመድ ሁኔታ ወይም በሥራ አካባቢም ከሆነ ያለው የሥራ ልምድ
- እምነት፣ ውስጣዊ ጥንካሬ፣ ችግርን የመቋቋም አቅም ...ወዘተ

ሲገናኙ → ውጤቱ

በግለሰቡ ላይ፡- ከቀላል እስከ ከባድ የጤና ቀውስ ላይ መውደቅ

በተቋማት ላይ፡- ከሥራ የሚቀሩ ሠራተኞች ቁጥር መበራከት፣ የሠራተኛ ፍልሰት መጨመርና ምርትና ገቢ መቀነስ ናቸው።

1.2 የውጥረት 'Stress' ዓይነቶች

በውጥረት ቁጥጥር ዘርፍ ላይ ታላቅ ሥራ በመሥራት ፋና ወጊና መሪ የሆኑት ዶ/ር ሐንስ ስሌይ የአእምሮ ዉጥረትን አዎንታዊና አሉታዊ በማለት በሁለት መልኩ ከፍለዉታል፡፡ (ሮቢንስ 1998፣ 664)

ሀ) አዎንታዊ ውጥረት 'eustress' or 'Positive stress'

- ጫዎንታዊ ውጥረት የመልካም አካባቢያዊ ለዉጦች ውጤት ነው፡፡ ይኸውም፡-
- ነገሮችን ወይም ችግሮችን የመቀበል አቅማችን ጠንካራ ሲሆን የሚከሰት የውጥረት ዓይነት ነዉ፡፡ በቀና አመለካከት ነገሮችን ስናይ ማለትም እወጣዋለሁ ብለን ስንቀበለው፡፡ ወይም
- ለማደግና ለመሻሻል ከበጎ ጎን አኳያ የሚታይ ውጥረት ነው፡፡ ይሄም ትርጉም ያለው ግብ ኖሮን ወደ ግባችን ለመድረስ ዛሬ እንዴት እንሥራ ከሚል የሚመነጭ፡፡

በደስታ ጊዜ የሚፈጠር ውጥረት ሎተሪ ማግኘት፣ ጋብቻ፣ የሥራ ዕድገት ማግኘት ወ.ዘ.ተ

ለ) አሉታዊ ውጥረት 'distress' or 'Negative stress'

ይህ ዓይነቱ ውጥረት አስጨናቂ ወይም አስፈሪ የአካባቢያዊ ለውጦች ውጤት ነው፡፡

- ችግሮችን ወይም ለውጦችን ስንፈራቸው፤ አክብደን ስ,ጋያቸው ወይም
- በጨለምተኝነት አመለካከት ራሳችንን ዝቅ አድርገን ችግሮችን የመቋቋም አቅማችንን ስናዳክምና ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ስንገባ የሚከሰት ነው፡፡

አዎንታዊው ውጥረት ግን ከተወሰነ ጊዜ በላይ ከቆየ ወደ አሉታዊ ውጥረት ይሸጋገራል፡፡ አሉታዊው ውጥረትም ለከባድ በሽታ ይዳርገናል፡፡ ስለዚህም አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ውጥረቶች ከበቂ እረፍትና መዝናናት ጋር ማመጣጠን አስፈላጊ ነው፡፡

የውጥረት አጠቃላይ መንስዔ በሕይወታችን ውስጥ የሚከሰት ማንኛውም ለውጥ ነው፡፡ ይኸም ለውጥ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ወጥረትን ይፈጥራል፡፡

በሥነ-ልቦና ምሑራን ጥናት መሠረት በውጥረት መለኪያ የተለኩት ለምሣሌ ያህል የተወሰዱ ጥቂት የደስታና የሐዘን ውጥረቶች ከዚህ በታች እንደሚከተሉት ቀርበዋል፡-

ምሣሌ ደረጃ		በደስታ ጊዜ ለተከሰተ የሕይወት ለውጥ ውጥረት መለኪያ 'Scale'		በሐዘን ጊዜ ለተከሰተ የሕይወት ለውጥ ውጥረት መለኪያ 'Scale'
1	ጋብቻ	50	የትዳር ጓደኛ በሞት መለየት	100
2	የልጅ ከቤት መውጣት (በጋብቻ፣ ወደ ኮሌጅ በመግባት ወዘተ)	29	ፍቺ	73
3	መሾም፣ መዛወር	29	ለእሥር መዳረግ	63
4	የላቀ የግል ስኬት	28	ከሥልጣን መውረድ	29
5	ዓመት በዓል ሲመጣ ወይም ግብዣ ለማድረግ ሲታሰብ	12	ቢሮ አካባቢ አእምሮ የሚረብሽ ሁኔታ ሲፈጠር (ከአለቃ ጋር ወይም ከሥራ ባልደረባ ጋር ግጭት ሲኖር)	23

ምንጭ፡ (ቲ ሞር,ጋን እና ሌሎችም ፣1993) ሳይቀናበር

III. የሥራ ውጥረት ወይም(Job stress)

የሥራ ውጥረት እንደማንኛውም ውጥረት መነሻው አብይ ምንጭ ነው፡፡ (ምዕራፍ I ይመልከቱ) በዚህ ጽሁፍ ትኩረት የተሰጠው በተለይ በሥራ አካባቢ በሚፈጠር የስራ ውጥረት ነው፡፡

2.1 በስራ አካባቢ የሚፈጠር የሥራ ውጥረት በሁለት ይከፈላል፡፡ (ፍራንሲሲ እና ጄን ሚል ቦርን 1980)

- ድርጅቱን (መ/ቤቱን) ከመፍራት የሚመነጭ
- ከሥራው የሚመነጭ

o ድርጅቱን ከመፍራት የሚመነጭ

- በድርጅቱ ውስጥ የሚካሄዱ ለውጦች የመዋቅር፣ የአሠራር፣ ቅርንጫፎችን የማጠፍ ወ.ዘ.ተ. ከመፍራት የሚመነጭ
- በድርጅቱ ውስጥ ያለሙት የዕድገት ቦታ ሲዘጋ፡፡

o ከሥራው የሚመነጭ፡-

- ግልጽነት የጐደለው አሠራር፡- ያለበቂ ሥልጠና መሥራት፣ ባልተሟላ የመሣሪያ አቅርቦት መሥራት ወ.ዘ.ተ.

- የሥራ ግጭቶች፡- ከተቀጠሩበት የሥራ ዘርፍ ውጪ ሌላ ሥራ እንዲሠሩ መገደድ ወይም ከሥነምግባር ውጪ ሞራልን የሚነካ ሥራ እንዲሠሩ መታዘዝ፡፡ እንዲሁም በተለያዩ አለቆች መታዘዝና ያልተመጣጠነ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ሲኖር፤ ወይም የአስተዳደሩ ዓይነት አምባገነናዊ ከሆነ፤ የሠራተኞችን እንቅስቃሴ በኮምፒውተር የሚቆጣጠር ከሆነ (ሞህቲንግ 1989).

የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሚያጋጥማቸው የሥራ ውጥረት መንስኤዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

2.1.1 የሥራ ኃላፊዎች የሚያጋጥማቸው የሥራ ውጥረት 'job stress'

የሥራ ኃላፊዎች የድርጅቱን ባህል ምሥል ከሣች ናቸው፡፡ ስለዚህም የድርጅቱን የሥራ ውጥረት ቁልፍ ማሳያም ናቸው፡፡ በሥራቸው ቦታ ፈገግታ እየራቃቸው፤ ግንባራቸውን እየከሰከሱ ከመጡ እነሱም ሆኑ ሠራተኞቹ በውጥረት ውስጥ ናቸው፡፡

የሥራ ኃላፊዎች የሥራ ውጥረት መንስኤዎች

የሥራ ኃላፊዎች የውስጥ ስብሰባ ሲበዛ፣ ለረዥም ጊዜ ያልተረጋጋ ሁኔታ ሲያጋጥም፣በ'ኢ-ሜል' ሥራን መከታተል እና ፈጣን ምላሽ መስጠት፣ በስልክ የሚሠሩ ሥራዎች ሲበዙ፣በኃላፊነታቸው ሁኔታዎችን መቆጣጠር ያለመቻል፣ ሲሆኑ ሌሎች የበታች ሠራተኞችም የሚጋሩት ደግሞ እንደ የቢሮ ፖለቲካ የሥራ ዋስትና ማጣት፣ የሥራ ቦታ ለውጥ፣ ደካማ ድርጅታዊ ግንኙነት፣ የተጨናነቀ ጊዜ፣ ቀጥተኛና ትክክለኛ የሥራ አቅጣጫ ያለመኖር ... ወዘተ

2.1.2 የሥራ ኃላፊዎች የሥራ ውጥረትን እንዴት ሊቋቋሙ ይችላሉ?

ውጥረትን ለመቀነስ የሚረዱ ዘዴዎች አንድ ወጥ አይደሉም፡፡ እንደ ችግሮቹ ሁኔታና እንደ ግለሰቡ ማንነት ይለያያሉ፡፡ ባብዛኛው ውጤታማ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን የሥራ ውጥረት ለመቆጣጠር የሚረዷቸው ዘዴዎች እንደሚከተሉት ቀርበዋል

- በሁሉም የኃላፊነት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሁሉ የሥራ ውጥረት መቋቋሚያ መንገድ

- ጊዜዎን ከፋፍለው ይመድቡ

ጊዜን በዕቅድ መጠቀም የሚለው አባባል አዲስ ነገር አይደለም፡፡ ብዙዎቻችን የምንስማው ግን የማንተገብረው ነው፡፡ እርሶስ ምን ያህል ተግባራዊ ያደርጉታል?

- ለእያንዳንዱ ሥራ እንደአስፈላጊነቱ ሰዓት ይመድቡለት፡፡ የተወሰነ ሥራ በጥራት ይሥሩ፡፡
- በቀን ውስጥ የተወሰነ ጊዜ ዕረፍት ይውሰዱ
- የምሣ ጊዜዎን በተቻለ መጠን ይጠብቁ፡፡ ምሣ ከበሉ በኂላ በሚመችዎት ዓይነት ትንሽ ዕረፍት ያድርጉ፡፡
- ሥራዎን በጥልቀት ይረዱ

የሥራ ኃላፊዎች ላይ የሥራ ውጥረት ከሚያስከትሉ ሁኔታዎች አንዱና ዋናው ቁልፉ በድርጅት ውስጥ ግልጽ ያልሆነ የሥራ አካሄድ መስፈን ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ከገጠመዎት ከበላይዎ ካሉት ጋር በግልጽ ተነጋግረው ተገቢና ግልጽነት ያለው የሥራ መዘርዝር (job description) እንዲኖርዎት ያድርጉ፡፡

- የማይሆነውን በግልጽ አይሆንም ማለትን ይድፈሩ

በአንድ ጊዜ ብዙ ሥራዎችን ለመሥራት በይሉኝታ ቃል አይግቡ፡፡

- የዓመት ዕረፍት መውጣትን ችላ አይበሉ

ብዙ ጊዜ አንድ ሠራተኛ አእምሮው በሥራ ሲወጠር ቤተሰቡንና በዙሪያው ያሉ ሰዎችን ይረሳል፡፡ መራራቁ ደግሞ በራሱ ሕይወትዎን ጣዕም የለሽ ሊያደርገው ስለሚችል ለቤተሰብዎና በዙሪያዎ ላሉ ሰዎች ጊዜ መስጠትን አይዘንጉ፡፡

- የተቋሙ ወይም የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ከሆኑ

ሠራተኞችን በቅርብ መከታተል ስሜታቸውን እንዲሁም ችግራቸውን ለመረዳት ያስችላል፡፡ የነሱ ችግር ሲቀረፍ በድርጅቱም ላይ ለውጥ ይመጣል፡፡ የድርጅቱ ዓይን ሠራተኞች ናቸውና፡፡ ስለዚህም በተወሰነ ጊዜ ዕቅድ አውጥተው ጠቅላላ ሠራተኞችን ይጎብኙአቸው፡፡ ቅሬታቸውንም ማዳመጥ ለመፍትሔ በር ከፋች ስለሆነ በተወሰኑ ወራት አንዴ ስብሰበው ቢያነጋግሯቸው የመቀራረብ ስሜትን ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም የድርጅቱ አጠቃላይ መረጃ ቀጥታ ከሠራተኞች እንዲያገኙ ይረዳዎታል፡፡

የተመቻቸ የሥራ ሁኔታ ለሥራ አነቃቂ እንደሆነ እሙን ነው፡፡ የሠራተኞች የሥራ ቦታ ምን ይመስላል? አቀማመጣቸውስ ለሥራ አመቺ ነው? ንፁህ አየር ይገኛል ወይ? ...ወዘተ የሚለው መፈተሽ አለበት፡፡

የድርጅቱን ዙሪያ ገባ ለማየት ዕቅድ ያውጡ (ሁሉን አወቅ ሥራ አስኪያጅ ውጥረትን የመቋቋም አቅም ስላለው ይተግብሩት (መጋዘኖች፣ ምድር ቤቶች፣ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ጓሮውንም ይቃኙ የተከመሩ አዲስና አሮጌ የድርጅቱ ንብረቶች ይኖሩ ይሆናል፡፡ እነዚህም ንብረቶች ገቢ የሚያስገኙ ወይም ወጪን ለመቀነስ ሊረዱ ይችላሉ፡፡

እንደዋና ሥራ አስኪያጅነትዎ የድርጅቱ ውድቀት መንስኤዎች ለእርሶም የሥራ ውጥረት ስለሚጨምሩ ለመቀነስ ይጣሩ፡፡ ይሄንን ጉዳይ የሚቆጣጠር ክፍል ከሌለ ወይም ከአቅሙ በላይ ከሆነ ሰዎችን ይወክሉ፡፡ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸውን ቀልጣፋ ሠራተኞችን በቡድን መልክ እንዲቋቋም ያድርጉ፡፡ ይሄንን ጉዳይ በቅርብ እንዲከታተሉ ሥልጣኑን ይስጧቸው፡፡ በማንኛውም መልኩ የንብረት ብክነትን ይቋቋሙ ፅዱ የሥራ አካባቢም ይሆን ዘንድ እገዛም አለውና፡፡

- ☐ ምንጊዜም በሥራ ቦታዎ ቀድመው ይገኙ፡፡ ለማለዳ ዜናዎች ጥቂት ደቂቃዎች ይመድቡ፡፡ በተቻለ መጠን ለዓለምና ለአገራዊ ዜናዎች የቀረቡ ይሁኑ፡፡ በተለይ የንግድ ድርጅት የሥራ ኃላፊ ከሆኑ የተፎካካሪ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ በንቃት ይከታተሉ፡፡ እነዚህ ነገሮች ለዕድገትም ሆነ ለውድቀት አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ የሕዝብ ግንኙነት ክፍልዎ ሠራተኞች በቂ የመረጃ መሰብሰቢያ ቁሳቁሶች ከሥልጠና ጋር እንዲያገኙ ይርዱ፡፡ በድህረ ገጽ ታግዘው ከሌሎች ድርጅቶች የሥራ ልምድ ትምህርት ይቅሰሙ፡፡

- የድርጅቱን የአሰራር ሁኔታ በቅርብ ይከታተሉ፤ አስተያየት ከተጠቃሚዎች በመውሰድ ለእርምትና ለስር ነቀል ለውጥ የተዘጋጁ ይሁኑ ከሠራተኞች ጋር በመሆን የተሻለ መንገድ ይቀይሱ፡፡

- በድርጅቱ ወይም በተቋሙ ውስጥ በአጠቃላይ የሠራተኞች የሥራ ውጥረት ካለ ምንጩን ተረድተው የሠራተኞችን የሥራ ብቃት አቅም በሙያ ሥልጠና ማዳበር(የውጥረት ቁጥጥር ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ(የሠራተኞችን ተነሳሽነት የሚጨምሩ እርምጃዎችን በመውሰድ ችግሮችን ለመቅረፍ መሞከርና የአሠራር ሁኔታን በመቀየር እንደሁኔታውና የችግሩ መጠን መተግበር፡፡

2.2. የሠራተኞች የሥራ ውጥረት መንስኤዎችና መፍትሔዎቹ

2.2.1. በሠራተኞች ላይ ውጥረት የሚፈጥሩ ሁኔታዎች

የሥራ ውጥረቱ ዓይነት	ምሣሌዎች
ውስን የሥራ ሁኔታና የሥራው ይዘት	ተደራራቢ ሥራ
	አሰልቺ ሥራ
	ረዥም የሥራ ሰዓት በዝቅተኛ ክፍያ
	አነስተኛና በቅድሚያ የማይታወቅ የእረፍት ጊዜ
	ተገቢ ያልሆነ የሥራ ውጤት መመዘኛ
ነባራዊ ሁኔታ	ጫጫታና የተጨናነቀ የሥራ ቦታ
	የታፈነ አየር
	ለጤናና ለአደጋ ተጋላጭ የሆነ ቦታ (መርዛማ ኬሚካሎች፣ ከባድ ዕቃዎችን ማንቀሳቀስ ወዘተ)
የድርጅቱ የአሠራር ደንብ	ግልጽ ያልሆነ ኃላፊነት ሲኖርዎት ወይም ሊያስጠይቀኝ ይችላል የሚባል ዓይነት አጠራጣሪ የሥራ ሁኔታ ሲኖር
	አንድ ሠራተኛ በብዙ አለቆች መታዘዝ
	ሠራተኛው የሚሠራውን ሥራ በሚመለከት ለውሳኔ ሰጪነት ተሳታፊ አለመሆን
	አመርቂ የሥራ ግንኙነት አለመኖር
የሥራ ቦታ ለውጥ	ከሥራ የመባረር ሥጋት ሲጨምር
	የሠራተኛ ፍልሰት ቁጥር እየጨመረ ሲመጣ
	ድርጅቱ ለሚያከናውነው ለውጥ ራስን ዝግጁ ያለማድረግ
	ዕድገት የማግኘት ዕድሉ ጠባብ ሲሆን
	ክፍልፋዩ የበዛ ትልቅ ሥራ የሚፈጥረው የመንፈስ ጭንቀት
እርስ በእርስ ግንኙነት	የአለቃና የሠራተኞች የሥራ ቦታ በጣም ሲራራቅ
	የበታች ሠራተኞች የሥራ ውጤት ደካማ ሲሆን
	በሠራተኞች መሐል የቢሮ ፖለቲካ፣ ውድድርና ቅራኔ ሲኖር
	ቁጣ፣ ዘለፋ፣ የመሳሰሉት ነገሮች ሲኖሩ
	ለረዥም ጊዜ ከቤተሰብ ርቆ መሥራት

ምንጭ፡- (ብርሃም፣ 1987:67)

2.2.2. የሠራተኞች የሥራ ውጥረት መፍትሔዎች

ሠራተኞች ራሳቸው ለሽንፈት የሚዳርጓቸውን ባህሪያትን ያስወግዱ

- **ራስዎን ይፈትሹና ያርሙ፡-** አዘውትረው የሚያረፍዱ ከሆነ ሰዓትዎን ሞልተው እንዲቀሰቅስዎት ያድርጉ፡፡ ጠረጴዛዎ በፋይል የተጣበበ ከሆነ የሚፈለገውን ብቻ አጠገብዎ ያድርጉት፡፡ ዕቅድ አውጥተው በቅደም ተከተል ይሥሩ፡፡

- **ፍጹምነትን እያለሙ አይጨነቁ፡-** ምንም ዓይነት 'ፕሮጀክት'ን ምንም ዓይነት ሁኔታ፣ ወይም ውሳኔ ፍጹም አይደለም፡፡ ፍጹምነትን ከእውነታው ውጪ ግብዎ ካረጉ እራስዎን እያስጨነቁ ነው፡፡

- **ጨለምተኛ አስተሳሰብዎን ያስወግዱ፡-** ለሁኔታዎችአሉታዊየሆነአመለካከትአያሳድሩ፡፡ የሥራ ተነሳሽነትዎን፣ በራስ መተማመንዎንና ችሎታዎን ያዳክምብዎታል፡፡

- **በድርጅቱ ውስጥ መድሎ የሚደረግብዎት ከሆነ መብትዎን ያስከብሩ፡-** በኢትዮጵያ የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 14(1(ረ ላይ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከትና በሌላም ሁኔታ በሠራተኛ መካከል ልዩነት ማድረግ ሕገወጥ ድርጊት መሆኑን አዋጁ ጠቅሷል፡፡ እንደዚህ ዓይነት መድልዎ ቢደርስብዎ መብትዎን በሕግ ማስከበር ይችላሉ፡፡

- **የሥራ መዘርዝር 'Job description'** ከሌለዎት ጠይቀው እንዲኖሮት ያድርጉ፣

- **እገዛ ይጠይቁ -** የቅርብ አለቃዎና የሥራ ባልደረቦችዎ ይተባበሩዎት ዘንድ ይጠይቁ፡፡

- **ወደ ሌላ ክፍል ይቀየሩ -** ሥራዎ ግን ውጥረት የበዛበት ቢሆንም መሥሪያ ቤቱን ወይም ድርጅቱን የሚወዱት ከሆነ ድርጅቱ ወደ ሌላ የሚመጥንዎት ቦታ እንዲቀይርዎት ይጠይቁ፡፡

- **ሥራ ይቀይሩ -** ሁሉም አማራጮች ካልሰሩ ለጤናዎ ሲሉ ሥራ ይቀይሩ፡፡

2.3. ለማንኛውም ሰው የሥራ ውጥረትን ለመቀነስ የሚረዱ የሥራ ውጥረት መቀነሻ ቴክኒኮች

እነኚህ ቴክኒኮች ቀላልና ዘወትር ልንከተላቸው የምንችላቸው ናቸው፡፡

- **ምግብዎን ያስተካክሉ**

- መመገብ ያለብዎት ምግቦች፡- ከፍተኛ የቫይታሚን ቢ-6 የያዙ (ድንች፣ ዓሣ፣ አጃ፣ ጥራጥሬዎች ወዘተ(ጉበት፣ ያልተፈተገ ጥራጥሬዎች፣ ሙዝ፣ 'ሲትረስ' የያዙ ፍራፍሬዎች እንደብርቱካን፣ ሎሚ፣ መንደሪን፣ ግሬፕ ፍሩት ወዘተ፣ ቸኮሌት በተለይ ጥቁሩ ቸኮሌት 'ማግኒዥየም' ስላለው መንፈስን ለማረጋጋት ይረዳሉ፡፡ ውሃ በብዛት መጠጣት፣ አልፎ አልፎ ደግሞ ከሞሚላን መጠጣት ሰውነትዎን ዘና ያደርጋል ካከታተሉት ግን ሱስ የማስያዝ ባህሪ አለው፡፡

ባጠቃላይ በአቅራቢያዎ የሚገኙ ቫይታሚንና ማዕድን የያዙ ምግቦችን ያዘውትሩ፡፡

- የሚከተሉትን ምግቦች አለመመገብ ወይም ማስወገድ

ምግብና መጠጦች	መመገብ የሌለብን ምክንያት
1. ሻይ፣ቡና፣ኮካኮላ	በውጥረት ጊዜ የበለጠ አነቃቂ መጠጦችን መውሰድ የለብንም ምክንያቱም ሰውነታችን ማረፍና በቂ እንቅልፍ ማግኘት ስላለበት ነው፡፡
2. ከባድ ምግቦች፣ ፈጥነው የሚደርሱ ምግቦች (በርገርና ሳንድዊች(እንቁላል አስኳል፣ ቅቤ፣ ዓይብ፣ ሥጋ፣ የኮኮናት ዘይት	ከፍተኛ ኘሮቲን፣ ቅባትና ካርቦሃድሬት ያላቸው በመሆናቸው የኮልስትሮል መጠንን ከፍ ስለሚያደርጉ፡፡ በጣም መቀነስ ወይም መወገድ አለባቸው በተለይ የእንቁላል አስኳል ከነጭራሹም አለመመገብ፡፡
3. ለስላሳና ሶዳ መጠጦች	እነዚህ ካርቦንዳይኦክሳይድ ያላቸው ስለሆኑ የደም ግፊትን ይጨምራሉ፡፡ ውጥረት ራሱ የደም ግፊትን ከፍ ስለሚያደርግ እነኚህ መጠጦች ደግሞ ውጥረትን ያባብሳሉ፡፡
4. ስኳርና ጣፋጭ ምግቦች	ውጥረት በደም ውስጥ የሚገኘውን የስኳር መጠንን ከፍ ስለሚያደርግ ተጨማሪ ስኳር ውጥረትን ያባብሳል፡፡
5. አልኮልና ሲጋራ	በአጠቃላይ የጤና ቀውስ ይፈጥራሉ፣ ሱስም ያሲዛሉ፡፡

ምንጭ፡ (ብርሃም፣153) ሳይቀናበር

- **አዎንታዊ ወይም ቀና አመለካከትን Positive thinking ያዳብሩ**

“The greatest discovery of my generation is that human beings can alter their lives by altering their attitude of mind. William James, psychologist” (እርካታ, ፌብሩዋሪ. 4-6, 2008)

ባለፉት ዓመታት ውስጥ አዎንታዊ ወይም ቀና አመለካከት ግድ የለሽ መሆን ነው የሚል ትርጉም ይሰጠው ነበር፡፡ እውነታው ግን ይሄ ሳይሆን በሳል አመለካከትን በመያዝ እራሳችንን ጭምር በቀናነት ማየት ነው፡፡ ከተማርኩትና ከተረዳሁት ልሠራው እችላለሁ ብሎ ማሰብ(እንዲሁም ሌሎችም ከተማሩትና ከተረዱት ሊሠሩት ይችላሉ፣ ችሎታችንንም ማካፈል ቀናነት ነው፡፡ ቀናነት መጥፎ ሁኔታዎችንና ችግሮችን ጊዜያዊ አድርጎ ማየትን ይጨምራል፡፡

ኢትዮጵያችን የሃይማኖተኞች አገር በመሆኗ አዎንታዊ አመለካከትን ለመተግበር ምቹ ሁኔታዎች አሉን፡፡ ምክንያቱም ማንኛውም ሃይማኖት ቅንነትና በጎ አሳቢነትን የሚያበረታታ ነው፡፡ በተጨማሪም ለጭንቀት፣ ለሐሣብ፣ ለሥጋት፣ ለፀፀት ለመሳሰሉ ሥነ-ልቦናዊ ችግሮች ፈውስ ለማግኘትም ይረዳናል፡፡ ኖርማን ቪንስንት የpositive thinking መጽሐፍ ፀሐፊ በፀሎት ሽክማችንን ለፈጣሪ አሳልፈን እንድንሰጥ ይመክሩናል፡፡

ለምሣሌ ደርግ የሶሻሊዝም ርዕዮተ-ዓለም አራማጅ ነበር፡፡ ቁስአካላዊ አመለካከት እንዲሰርጽ ሃይማኖተኝነትን የማጣጣል ሁኔታ ነበር የሚያካሂደው፡፡ በመጨረሻም ደርግ ለመውደቂያው ቀናት ሲቀሩት ግን የሚያደርገው ሲያጣ ሁሉም በየቤተእምነቱ ሙስሊሙም በመስጊድ ክርስቲያኖችም በየቤተክርስቲያናቸው ፀሎት እንዲያካሂዱ አበረታታ፡፡ በመገናኛ ብዙሃንም ከየቦታው ተላለፈ፡፡ የመጨረሻው የውጥረት ደረጃ ጭንቀት በአገሪቱ ነግሶ ስለነበር፡፡ ይህም የሚያሳየን ልናስወግደው ማንችለውን አስፈሪ ሁኔታ በፀሎት ራሳችንን ማረጋጋት መቻላችንን ሃይማኖትም ሆነ የሥነ-ልቦና ሳይንስም የሚደግፉት ነው፡፡

የሥነ-ልቦና ተመራማሪዎች እንደሚሉት በአዎንታዊ አመለካከት የመጀመሪያ ተጠቃሚው ግለሰቡ ራሱ ነው፡፡ ቀናነት ጤና ነው (ጠንካራ ወዳጅነት መመሥረቻም ነው፡፡ መረዳዳት መተጋገዝ ካለ ምርታማነት ይጎለብታል፡፡ ሲረዳዱና ችግርንም ሲካፈሉት ውጥረት ይቀንሳል ይላሉ፡፡

ቀናነት በውስጣችን በተፈጥሮ ባይኖረን እንኳን መማር የምንችለው ነገር ነው፡፡ በተቻለ አቅም ባለተስፋ (optimist) እንሁን አሉታዊ አመለካከት ወይም ጽላሎታዊ አመለካከት (pessimist) መሆን በራስ መተማመናችንን ያጠፋብናል፡፡ መጪውን ግዜ እንድንፈራውና ያለፉትን መጥፎ የሕይወት ገጠመኞቻችንን አጉልተን እያየን የዝቅተኝነት ስሜት እንዲሰማን ያደርጋል፡፡ ይሄ ደግሞ ለአእምሮ ውጥረት

ይዳርገናል። ያለፈ ስህተት ወይም ችግር ትምህርት ሆኖ ማለፍ አለበት እንጂ ጠቅላላ ሕይወታችንን ማጨለም የለበትም። ከአሉታዊው ሁኔታ የተገኘ ትምህርት ከአዎንታዊው አመለካከት ጋር ሲዋሃድ ሚዛናዊነት ይጎለብታል። ተስፋ መቁረጥና ሽንፈትም ይወገዳሉ።

የሥነ-ልቦና ሙሑሩ ዊልያም ጀምስ ስለ ቀና አመለካከት "የኔ ትውልድ ትልቁ ግኝት ሰዎች አመለካከታቸውን በመለወጥ ሕይወታቸውን ሊለውጡ መቻላቸው ነው።" ያሉት ለዚህ ነው እኛም አመለካከታችንን እንለውጥ። ይህም የሕይወት ለውጥ እንድናመጣ ያስችለናልና።

ሣቅ ወይም ፈገግታ አይለይዎት

የሥነ-ልቦና ሙሑሯ ኤልሣቤጥ ስኮት የሣቅን ወይም የፈገግታን ጥቅም እንደሚከተለው ታብራራዋለች።

- ሣቅ ሆሮሞኖችን ያነቃቃል፣ ያሳድጋል፣ ውጥረትን ይቀንሳል፣ የመከላከያ አቅማችንን ይገነባል፤አካልን ያፍታታል፤ ውስጣዊ አካል የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲስጥ ያደርጋል። በተለይ ከአንጀታችን የምንስቀው ሳቅ የመተንፈሻ አካላችንን፣ ትከሻችንን፣ ጡንቻዎቻችንን ያዝናናል፤ ልባችንም ሥራውን በአግባቡ እንዲሠራ ያግዛል፤ ቁጣን፣ ንዴትን፣ ውጥረትንና የመሳሰሉትን አሉታዊ ስሜቶችን ያስወግዳል። ሣቅ ማኅበራዊ ጥቅምም አለው። ለምሣሌ እከሌ ሳቂታ ነው ይባላል ሳቂታነት ከሰዎች ጋር በቀላሉ ያግባባል ሰዎች ስለእኛ መልካም ስሜት እንዲያድርባቸው ያደርጋል በአገራችን "ከፍትፍቱ ፊቱ" እንደሚባለው ሁሉ የቱንም ያህል ደግ ቢሆኑ ፊትዎት ካልተፈታ እንደ ክፉ ነው የምትታዩት። እናም ፈገግ ይበሉ፤ ሳቂታነት ነገሮችን ቀለል አድርገን በአዎንታዊ አመለካከት እንድናይ ይረዳል። በተጨማሪም ሳቅ ተላላፊ ነው ሲስቁ ሌላውም ፈገግ እንዲል ይጋብዙታል። (ኤልሳቤጥ፤ ማርች 2008)

የሳቅ ምንጮች

- ሳቅ ከትያትሮች፣ ከፊልሞች፣ ከሬድዮና ከቴሌቪዥን ኘሮግራሞች(ከየመዝናኛ ሥፍራዎች ይገኛል። ከጓደኛዎ ከቅርብ ሰዎችም፣ በራስ ከማሾፍም፣ ይሄ ሁሉ ሆኖ ሳቅ ሊመጣ ካልቻለ የውሸት ሳቅ ይሳቁ። የሥነ-ልቦና ሙሑራን የውሸት ሳቅም የእውነቱን ያህል ይጠቅማል ይላሉ። ለነገሩ የውሸት ሲስቁ አሳሳቅዎ ራሱ የእውነቱን ሳቅ ሳያመጣ ይቀራል ብለው ነው?

☐ እረፍት ያድርጉ

- እረፍት ይውሰዱ(ስለውጥረትዎ ያውሩ ያማክሩ(በሥራ ቦታ ከባልደረቦችዎ ጋር በመተባበር በመመካከር ይሥሩ(ውጥረትን በሚፈጥሩት ሁኔታዎች በራሱ ይቀልዱ።

• ስፖርት ይሥሩ

- የዮጋ እስፖርትን ይሥሩ ይህ በብዛት የሚመከር ነው። በጥልቀት በማሰብ በ'ሜዲቴሽን' ራስዎን ዘና ማድረግ ይማሩ፤ ውሃ ዋናም የሚወዱ ከሆነ ይዋኙ። በእግርዎ ይንሸራሸሩ በተለይ ወደማታ አየሩ ቀዝቀዝ ሲል ከባለቤትዎ ወይም ከፍቅረኛዎ ወይም ከሚወዱት ሰው ጋር እየተጨዋወቱ ቢጓዙም ጥሩ ነው ብቻዎን ሲሆኑ ችግርዎን የሚያስቡ ከሆነ ብቸኝነትን ይራቁት።

• በእረፍት ጊዜ ማሳለፍ በሚወዱት የዝንባሌዎ ዓይነት 'Hobby' ይዝናኑ

ለምሣሌ አትክልት መኮትኮት፣ ስዕል መሣል፣ ሙዚቃ መጫወት፣ ምግብ መሥራት ወ.ዘ.ተ ሊሆን ይችላል

• ጥሩ አለባበስ ይምረጡ

ልብስዎ አመለካከትዎንና ውስጥዎን የመቀየር ኃይል አለው። ጥሩ ሲለብሱ ሰዎች ለየት ባለሁኔታ ያይዎታል(ያደንቁዎታል። በተጨማሪም ከበሬታም ይሰጥዎታል። ያ ደግሞ ተቀባይነት የማግኘት መንፈስዎን ያዳብርሎታል።

IV. ውጥረት ጤና ላይ የሚፈጥረው ችግር

ውጥረት አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ ሥነ-ልቦናዊና በባህሪያችን ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድርብናል። ከቀላል የጤና ቀውስ እስከ ሞት ድረስ የሚያደርስ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል። መፍትሔ በጊዜ ካልተፈለገ እራሰን የመጥላትና የመግደል ችግር ሁሉ ያስከትላል። ከነኝህ ችግሮች በጥቂቱ እነሆ፡-

- ## አካላዊ የጉዳት ስሜቶች

ደረት ላይ የሚሰማ የመጫን ወይም የመጨቆን ስሜት፤ የምግብ አለመፈጨት፣ የእንቅልፍ ችግርና በጣም መድከም፣የመተንፈስ ችግር፣ ለደም ግፊት፤ ለስኳር፤ ለኩላሊት በሽታዎች መጋለጥ እንዲሁም የጡንቻ ሕመም፤ ለልብ ሕመም፤ራስምታት፤ ለጀርባና ወገብ ሕመም፤የቆዳ ሁኔታ መለወጥ፤ ከዚህ በፊት የነበረ በሽታ ወይም ‘አለርጂ’ ማገርሸት፣ ለካንሰር፤ ለተቅማጥ መጋለጥ፣ ለአልሰር፤ ለክብደት መቀነስ ወይም መጨመር፤ የሰውነት መከላከያ አቅም መዳከም እንዲሁም ሴቶች ላይ የወር አበባ ኡደት መዛባት ...ወዘተ ያስከትላል።

- ## ስሜታዊ ለውጦች

የስሜት መዋዥቅ፤ በራስ የመተማመንን ስሜት ማጣት፤የጭንቀት፣ የንዴት፣ የእፍረት፣ የድብርት፣ የፀፀት ሰሜቶች መታየት፤የመረዳት የመገንዘብ ችሎታ መዳከም፤ ብቸኝነት ወይም አጋዥ ረዳት ያጡ ሆኖ መሰማት፤የዝቅተኝነት ስሜት ማዳበር ...ወዘተ ያስከትላል።

- ## ባህሪያዊ ለውጦች

የሥራ ብቃት መዳከም፤ብዙ መተኛት፤ ብዙ መጠጣትና ማጨስ፤ ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀም፤ ብዙ የማነቃቂያ መጠጦችን መጠጣት ለምሣሌ ቡና፣ ሻይ፣ ኮካኮላ ...ወዘተ፤ ገለልተኛ መሆን፤ ብዙ መብላት ወይም የምግብ ፍላጎት ማጣት፤የወሲብ ፍላጎት ማጣት፤ በቂ እንቅልፍ ማጣት በቅዥት የተረበሸ ሌሊት ማሳለፍ ወይም፤ ስሜትን መግለጽ አለመቻል ...ወዘተ በውጥረት ሳቢያ የሚከሰቱ የባህሪ ለውጦች ናቸው።

ሥነ-ልቦናዊ ችግሮችና አሉታዊ ሃሣቦች

እኔ ውዳቂ ነኝ‘፤ ማንም ,የሚረዳኝ የለም‘ ፤‘ዕቃዬን የት እንዳስቀመጥኩ እንኳ እየረሳሁ ነው‘ ምን ማድረግ እንዳለብኝም አላውቅም‘ ... ወዘተ የሚሉ እራስን የመውቀስና የበታችነትን የሚያንፀባርቁ ሰሜቶች በውጥረት ሳቢያ የሚከሰቱ ሥነ-ልቦናዊ ችግሮች ናቸው።

ማስታወሻ

- ## ስለ ውጥረት ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፡-

በእርግጥ በውጥረት ውስጥ መሆንዎን ለማወቅ ራስዎን መፈተን ከፈለጉና ከችግርዎ መላቀቅ ካሻዎት ቀጥሎ ያለውን ድረ ገጽ ይመልከቱ።
http://www.cliving.org/lifestresstestscore.htm
ምን ያህል እንደተሰላቹ ለማወቅ ከፈለጉ ደግሞ http://www.mindtools.com/stress/Brn/Burnowtselftest.htm ይመልከቱ
ውጠረትዎን በድረ ገጽ በሚተላለፍ በጥልቀት ማሰብ ‘ሜዲቴሽን’ ትእዛዙን እየሰሙ ወይም እያነበቡ ዘና ማለት ከፈለጉ የሚከተለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ
http://www.mayoclinic.com/health/medtiation/MM00623

ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሣብ

ሰው ለመኖር ሥራ መሥራት አለበት። በሥራ ውስጥ ደግሞ ይብዛም ይነስም ውጥረት ይኖራል። ሰውነታችን በተፈጥሮ ውጥረትን እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ ቀስ በቀስ እየተላመደ ይሄዳል። መጠነኛ ውጥረት ለሥራ ለመጣጣር እገዛ ስለሚያደርግ አስፈላጊ ነው። እሱም አዎንታዊ ውጥረት ይባላል። ከመጠን ካለፈ ግን አሉታዊ ውጥረት ሆኖ የተለያዩ የጤና ቀውሶችን ያስከትላል።

ስለዚህም በሥራ አካባቢ የሚያጋጥም የሥራ ውጥረት ከአነቃቂነቱ አልፎ አስጨናቂ መሆን ደረጃ ላይ ከደረሰ መቆጣጠር መቻል ያስፈልጋል፡፡ በቁጥጥር ሥር ማዋል አልያም ማርገብ ተገቢ ነው፡፡ ከቁጥጥር ውጭ ከሆነ ግን ከጤና ጉዳቱም ባሻገር በተለይ በንግድ ተቋማት ላይ ኪሣራ ያደርሳል፡፡ በዚህ በውድድር ጊዜ ደንበኞችን መሣብና አብሮ መዝለቅ የንግዱ ሙያ ቁልፍ ተግባር መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ ለውጥረት ቁጥጥር ትኩረት መስጠት ግዴታ እየሆነ ነው፡፡ ምክንያቱም በውጥረት የተሞላ፣ የተሰላቸና የከፋው የሠራተኛና የሥራ ኃላፊ ደንበኞችን ደስ ብሎት አያስተናግድም፡፡ ይህም ደግሞ ደንበኞችን ያሸሻል፤ ገቢን ይቀንሳል፤ ብሎም ድርጅቱን ለውድቀት ከሚዳርጉት መንስኤዎች እንደ አንዱ ይሆናል፤ ስለዚህም የሀገሪቱን አጠቃላይ ብሔራዊ ምርትም ይጐዳል፡፡

ማንኛውም ሰው በውጥረት መያዙንና ምን ያህል ደረጃ ላይ እንዳለ ለማወቅ ከፈለገ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ተጨማሪ መረጃ ላይ በተጻፈው መሠረት ራሱን መፈተሽና ውጥረትን ማርገቢያ ቴክኒኮችን በመተግበር ራሱን ከውጥረት አደጋ መጠበቅ ይችላል፡፡

በተጨማሪ ደግሞ ተቋማት ከኪሣራና ከተለያዩ ችግሮች ለመዳን ለሠራተኞቻቸው ውጥረትን እንዴት መቋቋም እንደሚችሉ ሥልጠና መስጠቱ አስፈላጊ ነው፡፡ ሆኖም መጀመሪያ ድርጅቶች በውስጣቸው ያለውን የሥራ ውጥረት መጠን መፈተሽ አለባቸው፡፡ ውጥረቱ ገደቡን ከጣሰ ምንጩን መረዳት ነው ይኸውም፡-

- ሥራው የወለደው ከሆነ የውጥረት መቀነሻ መፍትሄዎችን መተግበር፡፡
- ከሠራተኛው የግል ችግር ወይም ከቤተሰቡ ጋር በተያያዘ ምክንያት የተፈጠረ ከሆነ ለቤተሰብ ችግሮች በሚሰጥር የምክር አገልግሎት ቢሰጥ፡፡
- የገንዘብ ችግር ከሆነ ደሞዝና ኑሮ ካልተጣጣመ ድርጅቱ የብድር አገልግሎቶችን ለሠራተኞች ቢሰጥ፡፡ እንዲሁም
  - ♦ መሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎችን ከአምራቾች በብድር የሚገዙበትን መንገድ ማመቻቸት፡፡ በተጨማሪም ሌሎች በጥናት የተደገፉ እርምጃዎች ቢወሰድ መፍትሔ ይሆናል፡፡

የውጥረቱ መንስኤ ካልታወቀ፡- ድርጅቱ የአሠራር ሁኔታውን መቀየር አለበት፡፡ ይኸውም ከሠራተኞች ጋር በመመካከርኛ ሠራተኞችን በውሳኔ ሰጭነት በማሳተፍኛ ማህበራዊ ግንኙነት በአግባቡ እንዲሰርጽ እገዛ በማድረግኛ ሠራተኖችን ከቦታ ቦታ በማዘዋወርኛ ሥልጠና በመስጠት ችሎታቸውን ማዳበርኛ ሽልማትና ማበረታቻ መስጠት፤ ሽልማት ጎሽ ጥሩ ሰርተዋል ከሚለው አረፍተ ነገር ይጀምራል፡፡ የምስጋና ደብዳቤ በግል ማህደር ከማኖር ቀላል ከሚመስሉ ነገር ግን የሠራተኛውን ተነሳሽነትን በከፍተኛ ደረጃ ከሚያሳድጉት ጀምሮ ድርጅቱ አቅሙ የፈቀደውን ነገር በማድረግ አሰራሩን ቢቀይር ጥሩ ነው፡፡

ድርጅቱ ሊያስወግዳቸው የማይችላቸው ዓይነት የሥራ ውጥረት ከሆኑ፡-

ድርጅቱ ለሥራ ኃላፊዎችና ለሠራተኞጨክችግሩ ጋር ተስማምተው እንዴት መኖር እንደሚችሉ የውጥረት ቁጥጥር ሥልጠና እንዲያገኙ ቢያደርግ ችግሩን ለመቋቋም ትልቅ እገዛ ይኖረዋል፡፡

በአጠቃላይ ይህንን የሥራ ውጥረት ለመቀነስ የሚረዳ ሥልጠና በስፋት በአገሪቱ ውስጥ ቢሰጥ ችግሩን በተወሰነ ደረጃ ለመቅረፍ ይረዳል፡፡

ዋቢ መጽሐፍትና ድረ ገጾች

Berham Nana, (1967) Stress Management Tools, 1967

Elizabeth Scott "The stress Management and Healthe benefits of Laughter"
http:// stress.about.com/od/stresshealth/a/laughter.htm (March, 2008)

ERKATA Plc, (2008) "Managing Towards excellence Supervisory and Managerial Effectiveness Training handout," February 4-6, Addis Ababa

Francis G. James and Gene M, (1980)_ Human Behavior in The Work Environment, Good year Publishing Co. Inc. Santa Monica

Mhoting ELSE Smudge, (1989) organization Behavior, star Publishing Co,

Robins Stephen P. (1998) Organizational behavior 8th prentice Hall upper saddle Rivers, New Jersey 07458

T. Morgan C. Richard A. king , John R.W and John s. (1993) Introduction to Psychology, 7t ed. Tata Mc Graw, Hill edition, 1993

Vincent Norman Peale, (2004) The Power of Positive Thinking, 3rd ed Eburg Press,

http://www.cliving.org/lifestresstestscore.htm

http://www.mindtools.com/stress/Brn/Burnowtselftest.htm
http://www.mayoclinic.com/health/medtiation/MM00623
የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 377/1996 በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ አንቀጽ 14(1)ረ

ሙዳየ ቃል

የቢሮ ፖለቲካ - በቢሮ አካባቢ በጓደኝነት፣ በዝምድና፣ በዘር፣ በፆታዊ ግንኙነት ... ወዘተ የሚፈፀም አድሎ

ረግዞችም ጫሮች

(ከአበበች ድሪባ)

የምሽቷ ሙሉ ጨረቃ በመስኮቱ መስታወት ስትታይ ውጭውን ብርሃንማ ሌሊት አድርጋዋለች፡፡የጥናት ሰዓቷን የሚያስታውሳት የማንቂያ ደወል ደጋግሞ ይጮሃል፡፡ ብሌን ከእንቅልፏ ነቅታ ዓይናቿን እየጠራረገች ወደ ግድግዳው እጇን ሠነዘረች፡፡ ማብሪያ ማጥፊያውን ደጋግማ ሞከረች፡፡ የኤሌክትሪክ ኃይል ባለመኖሩ ሙከራዋ አልተሳካም፤ በብርድ ልብሷ ሽፍንፍን ብላ የተቋረጠውን እንቅልፏን ለመጨረስ ተመልሳ ተኛች፡፡

በዝናቡ ምክንያት ካለወትሮዋ አርፍዳ ነው የተነሳችው፡፡ ከትምህርት ዓለም የመጀመሪያዋ ወደሆነው የቢሮ ሕይወት ለመሄድ ትጣደፋለች፡፡ ወንድሟ ዳንኤል ጥድፊያዋን እያየ «እኔም አልረፈደብኝ! በሰዓት ስንት ይከፈልሻል?» አላት በቀልድ ቅላጼ፡፡ እንደወትሮው ቁርስ ላይ ከወንድሟ ጋር አልተቀላለደችም ፤ ፍዝዝ ብላለች፡፡

« ምን ሆነሻል ብሌን ?» አለ ዳንኤል

« ደብሮኛል! ለምን ቅር ቅር እንደሚለኝ አላውቅም ዳኒ» አለችው፡፡

« ኦ! ዛሬ ወደ ትምህርት ቤት ሳይሆን ወደ ሥራ ስለምትሄጂ ተለማማጅ ብሌን ድብርት ይቅራ!» አለና ጀርባዋን መታ መታ አደረጋት፡፡

« አንተ ምን አለብህ! » አለችና ተሰናብታው ወጣች፡፡

መስፍን መልከ መልካም፣ በሃምሳዎቹ አጋማሽ የሚገኝ ጐልማሳ ነው፡፡ ሽበቱን ለመደበቅ በቀለም እያሳመረ በአጭሩ የሚከረከመው ፀጉሩ፣ በቁንጥ ከሚላጨው ፂሙ ጋር ተዳምረው ልዩ ውበትን አጐናጽፈውታል፡፡ቁመናው ዕድሜውን ስለማያሳብቅ 'ኤቨር ግሪን' ይሉታል በቅርብ የሚያውቁት፡፡ ከሰዎች ጋር የሚግባባና ቀልድ ዐዋቂ ነው፡፡ አንድ ነገር ላይ ማትኮር እምብዛም አይወድም፤ ስልችት ይለዋል፡፡

ቢሮው ውስጥ ተቀምጦ ፋይሎችን ያገላብጣል፡፡ በአራት ሰዓት ኃላፊው ቢሮ ስብሰባ ስላለው ያዘጋጀውን ጽሑፍ በለሆሳስ ያነባል፡፡ «ጥሩ ነው!» አለ፤ ባዘጋጀው ጽሑፍ ተደስቶ፡፡
የቢሮው በር ተንኳኳ፡፡ « ይግቡ!» አለ፡፡ መስፍን፡፡ ቀጠን፣ ረዘም ያለች ወጣት ገባች፡፡ መስፍን ከመቀመጫው ብድግ ብሎ «ጤና ይስጥልኝ» አላት፡፡ ወጣቷ አፀፋውን መለሰች፡፡ እንድትቀመጥ ጋበዛት፤ ስትቀመጥ አጭር ቀሚሷን ሳብ ሳብ አደረገች፡፡

እግሯ ያምራል፤ «እንዴት ውብ ነች?» እያለ ከፊት ለፊቱ ያለችውን ወጣት ዓይኗ ውስጥ ትክ ብሎ አያት፡፡ ዓይኗ ልዩ ውበትን አጎናጽፏታል፡፡ ቅንድቦቿ ግጥም ያሉ ናቸው፡፡

«ምን ልርዳሽ? » አላት መስፍን፡፡

«ደብዳቤ ወደዚህ ክፍል ተመርቶልሻል ተብዬ ነበር!»አለች ብሌን፡፡ ድምጿ ሙዚቃዊ ቃና ፈጥሮበታል፡፡ መነጽሩን እያስተካከለ

«ጉዳዩ ምን ነበር?» አለ ተሽከርካሪ ወንበሩ ላይ ለጠጥ በማለት፡፡

«ከት/ቤት የሥራ ላይ ልምምድ ለማድረግ የተጻፈልኝ ደብዳቤ...» አላስጨረሳትም፡፡ «አው! ትክክል ደርሶኛል፡፡» አጠገቡ ከተቀመጠው የወረቀት ትሪይ አንዱን በማንሳት

«ስምሽ ማነው?»

«ብሌን ታደሰ» አለችው፡፡

«የአካውንቲንግ ተማሪ ነሽ? »
«አዎ» አለች፡፡

በደብዳቤው ላይ የሆነ ነገር ጻፈበት፡፡ ሰዓቱን መልከት አደረገ፡፡ ለአራት ሰዓት አስር ጉዳይ ይላል፡፡ ሰዓቱ ላይ አፈጠጠ፡፡ ስልሳ ደቂቃ መሆኑ ቀረ? ወይስ...»አለ ለብቻው፡፡ አጠገቡ ካለችው ቆንጆ ጋር መለያየት አልፈለገም፤ በመጨረሻ የግዱን«ይቅርታ! ብሌን ነገ ብትመለሺ፤ ለማንኛውም መደወልም ይቻላል፡፡» የቢሮውን ስልክ ነገራት፡፡ «አመሰግናለሁ» ተሰናብታው ወጣች፡፡ በሩን ከፍታ ስትወጣ ልቡ አብሯት ሄደ፡፡ ስለብሌን እያሰላሰለ ጥቂት ደቂቃዎች አሳለፈ፤ የስብሰባው ሰዓት በመድረሱ ያዘጋጀውን ጽሑፍ አንስቶ ወደ ኃላፊው ቢሮ ሄደ፡፡

በሰዓቱ ስራው ላይ መገኘት የሚወደው መስፍን ዛሬም እንደወትሮው ማልዶ ገብቷል፡፡ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ከአርባ አምስት ነው፡፡ የስልኩን እጀታ አንስቶ
« ነኝ! እንዴት ነሽ ብሌን፣ ጉበዝ ተማሪ ከወዲሁ ያስታውቃል፡፡
« እንዴት! » አለች ብሌን
« የቤት ሥራውን ተጠንቅቆ ይሠራላ ቂ...ቂ...ቂ... » አለ፡፡
« አቤት! » አለች ብሌን 'አልገባኝም' በሚል ምጸት፡፡
« ዛሬ መጀመር ትችያለሽ፡፡ »
« እሺ፡፡ » ብላ ስልኩን ዘጋች፡፡
«የምን የቤት ሥራ ? ምንድነው የሚሉት ሰውየው፡ አለች ለብቻዋ፡፡ በቀጠሮዋ መሠረት ልምምድ ወደምታደርግበት መሥሪያ ቤት እንደደረሰች የመስፍንን ቢሮ በቀስታ በማንኳኳት ወደ ውስጥ ገባች፡፡መስፍን ሲያያት ፈገግ ብሎ ለሰላምታ እጁን ዘረጋ፤እሷም አፀፋውን መለሰች፡፡ እንድትቀመጥ ጋበዛት፡፡

«መሥሪያ ቤታችን በርካታ እንዳንቺ ያሉ ወጣት ተማሪዎችን ተቀብሎ ሙያቸውን እንዲያዳብሩ በማድረጉ ረገድ ጥሩ ውጤት አስመዝግቧል፡፡ አንቺም በልምምድሽ ወቅት በርካታ ቁምነገሮችን እንደምትቀስሚ ተስፋ አደርጋለሁ» አላት፡፡ራሷን በመነቅነቅ ምላሿን ሰጠች፡፡ከወረቀት ትሬይ ውስጥ ደብዳቤውን አንስቶ

«አሁን ለጊዜው ፋይናንስና በጀት ክፍል ተመድበሽ ልምምድሽን ትጀምሪያለሽ፡፡
« ሌሎች የሚያጋጥሙሽ ችግሮች ካሉ አማክሪኝ... እንረዳዳለን፡፡
«ወደተመደብሽበት ክፍል ከመሄድሽ በፊት ሻይ ቡና!» አላት፡፡
«አሁን ጠጥቻለሁ አመሰግናለሁ!» አለች፡፡
«የቢሮአችን በጣም አሪፍ ነው ሞክሪ»
«እግዚአብሔር ይስጥልኝ!» አለች በድጋሚ፡፡»

የወሩ የሂሳብ መዝጊያ በመሆኑ የክፍሉ ሠራተኞች ሥራ የበዛባቸው መሆኑ ከድርጊታቸው ያስታውቃል፡፡ ብሌን በዓይኗ ቃኘት አደረገቻቸው አንደኛዋ «ይቅርታ አስቸኳይ ሥራ ስላለብን ነው፤ እስከዛው አንብቢ» ብላ አጠገቧ ያለውን መጽሔት ሰጠቻት፡፡ አመስግና ተቀበለቻት፤ጥቂት ገጾች እንዳገላበጠች መስፍን በሠራተኞች የሥራ ብዛት ሰበብ በማድረግ የውስጥ ስልክ ደውሎ አስጠራት፡፡ መልዕክት የተቀበለችው ሠራተኛ ብሌንን መስፍን እንደሚፈልጋት ነገረቻት፡፡ ቢሮውን ከፍታ ስትወጣ፣
አይ! መስፍኔ እንደወረዱ መቅለብ የሚያቆመው መቼ ነው?»አለች፡፡ መልዕክቱን ያስተላለፈችው ሌላኛዋ «የመጨረሻውን ሲገላገል ነዋ! »
«እሱ የመጨረሻውን እስኪይዝ ስንቶቹ በሱ ይሰናከላሉ፣ ጠቦት እንደታዘዘለት በሽተኛ ትንንሽ ልጆችን...»አለች በቁጭት፡፡

ኮምፒውተሩ ላይ የሚሠራው ጓደኛቸው ንግግራቸውን እያዳመጠ «እዚህ ብቻችሁን ከምትነጋገሩ አትመክሩትም! »

ማንን ነው የምንመክረው እባክህ!እንዴት ታሾፋለህ? አለች የመጀመሪያዋ ተናጋሪ፡፡

ወደ መስፍን ቢሮ ተመልሳ እንደገባች « ዛሬ ሥራ በዝቶባቸዋል ነገ ትጀምሪያለሽ» አላት፥፥

«ሲሰሩ ብመለከትም ደስ ይለኛል» አለችው፡፡

«መሥሪያ ቤታችን ተለማማጆች ዘና ብላችሁ ሥራችሁን እንድትሠሩ ይፈልጋል፡፡»

«እንዴት?»

« መጨናነቅ የለባችሁማ፡፡»

በአግራሞት ተመለከተችው፡፡ ለጥቂት ጊዜያት ክፍሉ ውስጥ ዝምታ ሰፈነ፡፡ በዝምታው መካከል የሞባይል ጥሪ ተሰማ፡፡መስፍን ንግግሩን እንደጨረሰ

« በቃ አሁን ልሂድ አይደል?» አለችው፡፡

«እሺ ብሌን ነገ በ2፡30 ሥራሽ ላይ» አለ ሞባይሉን እያስቀመጠ፡፡

«ደህና ዋሉ» ብላ ተሰናብታው ወጣች፡፡

ከቢሮው ወጥታ ወደ ቤቷ ስትሄድ ደግሞ «ዘና ብላችሁ፣መጨናነቅ የለባችሁም ምን ማለት ነው? ሰውየው አስተያየታቸው አይመችም» አለች በሀሳብዋ፡፡ ወደ ቤቷ እንደደረሰች ሥራ ባለመጀመሯ ለምን ያመላልሱኛል፣ስደውልላቸው ነገ ነይ አይሉኝም ነበር! አለች በቅሬታ፡፡ ማታ ከቤተሰቧቿ ጋር ለእራት ስትታደም ወንድሟ ዳንኤል ስለ ቀን ውሎዋ ጠየቃት፡፡ ዛሬ አለመጀመሯን ተናገረች፡፡

ወንድሟ ዳንኤል ማታ ከሥራ ሲመለስ ብሌንን ስለ ቀን ውሎዋ ጠየቃት፡፡ ዛሬ አለመጀመሯን ነገረችው፡፡

« ለምን አልጀመርሽም?» አላት

« ኃላፊው የአንድ ቀን ፈቃድ ሰጡኝ» አለች እየሳቀች፡፡

« ፈቃድ !አሉ እናትና አባቷ በግርምት

« ሞዛዛ የምን ፈቃድ?» አላት ዳንኤል፡፡

« ለእናንተ ብቻ ነው እንዴ ፈቃድ፣ ለተለማማጅም ሥራ ስንገባ የሚታሰብ ፈቃድ ይሰጣል መሰለኝ¡» አለች በምፀት አነጋገር፡፡ ሁሉም ሳቁ፡፡

« ጨዋታ ጨምረሻል»አላት ወንድሟ፥

«የመሥሪያ ቤቱ ደንብ ቢሆን ነዋ! ነገ ነው የምትጀምሪው ብለውኛል ውነቴን ነው» አለች፥

እንዲህ እየተቀላለዱ በአንዳንድ መሥሪያ ቤቶች ያለውን ሁኔታ ከእናቷ፡ከአባቷና ከወንድሟ እያዳመጠች እራታቸውን በልተው ጨረሱ፡፡ ብሌን ከቤተሰቧቿ ጋር በነጻነት ስለምትነጋገር በራስ የመተማመን ክሂሎቷ ከፍተኛ ነው፡፡ የተሰማትን በግልጽ ትናገራለች፡፡

✷ ✷ ✷ ✷ ✷

ብሌን የሥራ ሰዓቷን አክብራ በየጊዜው ልምምዷን ታከናውናለች፡፡ በክፍሉ ውስጥ ያሉት ሰራተኞች ለማወቅ ካላት ጉጉት የተነሳ የምትጠይቀውን ጥያቄ ስለሚያስረዷት፣ የተለያዩ አሠራሮችን በአጭር ጊዜ ለማወቅ ረድቷታል፡፡

መስፍን በሻይ ሰዓት ደውሎ ጠራት፡፡ የቢሮውን በር አንኳኩታ እንደገባች ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ተቀበላት፡፡

« ሥራ እንዴት ነው?»

« ጥሩ ነው»

« ከሠራተኞች ጋር ችግር አለ ? »

« በጣም ጥሩዎች ናቸው፤የምጠይቀቸውን ያስረዱኛል»

« በደረቁ ጨቀጨቅሁሽ ሻይ ቡና!»

« ጠጥቻለሁ፡፡»

« ዛሬ የደመወዝ ቀን ነው ምሣ አብረን እንበላለን! » አለ፤ ፊት ለፊት እያያት፡፡

« አመሰግናለሁ»አለች፡፡

« የትራንስፖርት አበል እንኳን በሌለበት፣ ለመሥሪያ ቤታችን የነፃ አገልግሎት እየሰጠሽ ቢያንስ እንኳን አንዳንድ ቀን ምሳ መጋበዝ ያንስብሻል!»

« ከመሥሪያ ቤታችሁ ያገኘሁት ልምድና ዕውቀት ገንዘብ የሚገዛው አይደለም፡፡» ምላሿ ገርሞታል፡፡

«የምን ምሳ? ለምን!»አለች ለብቻዋ፡፡

ሌላ መልስ ላለመስማት በሚፈልግ ፍጥነት፣

«ብሌን መልካም ሥራ በ6፡30 እንገናኝ» አላት፡፡

«ፈቃድ አይጠየቅም እንዴ! » አለች፡፡ በለሆሳስ

እያመነታች «እሺ» ብላው ከቢሮው ወጣች፡፡ወደ ቢሮዋ ስትመለስ

«ፋዘርን ምን አሳሰባቸው? አበል ምናምን የሚሉት እሚዘዛለሁ ቢሉ ግን ልካቸውን ነው የምነግራቸው» አለች፡፡ የምሳ ሰዓት ደርሶ ሁሉም ከቢሮው ወደ ምሳው ይጣደፋል፡፡ መስፍን ኮሪደሩ ላይ ይንጎራደዳል፤ ብሌን ዘግየት ብላ ነው የወጣችው፡፡ መኪናውን አስነስቶ ለምሳ ሄዱ፡፡ምግብ ቤቱ በሰዎች ተጨናንቋል፡፡ አንድ ጥግ ላይ ቦታ አግኝተው ተቀመጡ፡፡ አስተናጋጁ ሥራ የበዛበት መሆኑ በእንቅስቃሴው ያስታውቃል፡፡ መስፍን ከምግብ ዝርዝር መምረጫው ላይ የመረጡትን ምግብ ለማዘዝ አጨበጨበና

«ታዘዘን!»አለው፡፡

አስተናጋጁ ያዘዙትን ምግብ በፍጥነት ይዞ መጣ፡፡ እሱ ብዙ እየተናገረ፣ እሷ እያዳመጠች ምሳቸውን በልተው ጨረሱ፡፡ ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል በመካከላቸው ዝምታ ሠፈነ፡፡

«የት ነው ሠፈርሽ?»

«ልደታ!»

«ከመሥሪያ ቤታችን ሩቅ ነው አይደል?» አለ፤ ርቀቱን እንደማያውቅ ሁሉ፡፡

« አንድ ታክሲ ነው የምይዘው፣ ብዙ አይርቅም፡፡»

« የታክሲ ወጪውም ቢሆን ምንም ለማይከፈላት ተማሪ ከባድ ነው፡፡»

«ብዙ አላወጣም ጠዋት አባቴ ያደርሰኛል፡፡»

« ከሥራ በኋላ ደግሞ እኔ ተረኛ ልሁና!»

« አመሰግናለሁ!»

« ወንድሞች፣ እህቶች አሉሽ?»

«አዎ፡፡»

«ቅፅ የሚያስሞሉ ይመስላል!» ብላ በመጣላት ሀሳብ ፈገግ አለች፡፡

ወደ መኪናው ሲገቡ ፣

« ብሌን እ.ወ.ድ.ሻ.ለ.ሁ»አላት

«እንዴ!» አለች ድምጿን ከፍ አድርጋ፡፡

«ይገርምሻል!ልጄን ትመስይኛለሽ» ብሎ እጁን ጭኖችዋ ላይ አሳረፈ፡፡

ከመቅጽበት እጁን አስለቅቃ« ልጅዎትን ከመሰልኩዎት እንደ ልጅዎ እዩኛ፡፡» አለች ኮስተር ብላ፡፡

« ምን አልሽ!» አለ፡፡ እንዳልሰማ በሚመስል ቅላፄ

«ብሌን ሙች ከልጄ በላይ!» አለና ቀኝ እጁን ትከሻዋ ላይ አደረገ፡፡»

« እኔ እኮ እንደ አባት ስላየሁዎት ነው የምሳ ግብዣዎን የተቀበልኩት እንጂ…» ብላ በድጋሚ እጁን ከትከሻዋ ላይ አወረደችው፡፡ «ምን ዓይነት መጥፎ ሰው ናቸው» አለች ለብቻዋ፡፡

«ብሌን ምን አጠፋሁ?»

« ትልቅ ሰው አይደሉ? ስለ ሴትልጆች ያልዎት አመለካከት ጥሩ አይደለም፡፡»

«ተሳስተሻል! ብሌን ሴቶችን እንዴት እንደምንከባከብና እንደምወዳቸው አታውቂም»

«ይቀልዳሉ?»

«የምን ቀልድ አመጣሽ እውነቴን ነው፡፡»

«እኔ ግን ከእርስዎ ይህን አልጠብቅም አዝናለሁ!»

«ኃይለኛ ነሽ» አላት፡፡

«የሩቅ ህልሜና የአባቴ ቃል በራስ መተማመን እንዲኖረኝ አግዘውኛል»

«እንዴት?»

«‘ጫፍ የወጣ ሁሉን ያያል’» ይለኛል፡፡

«ምን ማለት ነው? ፍልስፍናሽ አልገባኝም»

«በጣም ቀላል ነው»

«የኔ ቆንጆ ክርክር ትችይበታለሽ፤ ከአካውንቲንግ ይልቅ ሕግ ነበር ማጥናት ያለብሽ፡፡» አላት፡፡

ጥቂት እንደተጓዙ ሞባይሉ ጥሪ አሰማ፡፡ ለረዥም ደቂቃዎች የስልክ ምልልስ ያደርጋል መስፍን፡፡ ብሌን በሀሳቧ ሩቅ ነጐደች፡፡ ባለፈው ዓመት በክፍል ውስጥ ያጋጠማት፤ የአካውንቲንግ መምህሯ ትውስ አሏት፡፡

በትምህርቷ ጎበዝ ከሚባሉት ምድብ ውስጥ ናት፡፡ ነገር ግን በመምህራኖቿ የሚደረግላት አላስፈላጊ ድጋፍ ያበሽቃታል፡፡ በክፍል ውስጥ ሁልጊዜ በመጠየቅ፣እንዲሁም የተሰጣትን የቤት ሥራ በመሥራት፣ በቡድን ሥራና ጓደኞቿን በማስጠናት ትታወቃለች፡፡ያልገባትን ከመጠየቅ አትቦዝንም፣ ነገር ግን በፈተና ጥሩ ውጤት እንደምታመጣ በመተማመን የሠራችውን መምህሩ በሦስተኛው ቀን ለተማሪዎች የመልሰ ወረቀት ሲመልሱ የብሌን ስም አልተጠራም፡፡ ብሌን እጅዋን አውጥታ፣ የመልስ ወረቀት አልተሰጠኝም!» አለች፡፡

«ተፈትነሻል?» ጫሏት መምህሩ፡፡

«አዎን»

«አሁን ሌላ የመልስ ወረቀት የለኝም፤ መፈተንሽን በምን አረጋግጣለሁ!»

«በዕለቱ የፈረምኩበት የስም ዝርዝር አለ አይደል! »

«ተፈትናለች» አለ፡፡ አጠገቧ የተቀመጠው ተማሪ

«ማን ጠየቀህ? እሷ ለመናገር መች አነሰች!» አሉ፡፡ ቆጣ ባለ ድምፀት

«ጭሁን በጥያቄው ላይ ያላችሁን አስተያየት እንነጋገር፤ ከክፍለጊዜው በኋላ አናግሪኝ » ብለው ለተማሪዎቹ እድል ሰጡ፡፡

«ብሌን የአንቺን ፈተና በቃለ መጠይቅ መልክ ሊያደርጉት ነው መሰለኝ!» አለ የቅድሙ ተማሪ፡፡ አጠገቡ ያሉት ሁሉ ሳቁ፡፡ ብሌን ተናዳለች፡፡

ክፍለጊዜው ሲያልቅ ከጓደኛዋ ጋር ተከትላቸው ወደ ቢሮ ሄደች፡፡ ሁለት መሆናቸውን ሲያዩ፣

«ጉዳይህ ምን ነበር?» አሉት ተማሪውን

«ከብሌን ጋር ነው የመጣሁት! » አለ በግዴለሽነት አነጋገር፡፡

«ከክፍል ውስጥ ጀምሮ ትበጠብጣለህ!» ብለው ገርመም አደረጉት፡፡ ቀጠል በማድረግም« ውጭ ጠብቃት! » አሉት፤ ተማሪው ቢሮአቸው ውስጥ መምጣቱን ባልወደደ ስሜት፡፡ ብሌን በዓይኗ ጠቀሰችው፣ አብሯት እንዲቆይ፡፡ ተማሪው በመሃል አንዴ ብሌንን አንዴ አስተማሪውን እያየ ይንጉራደዳል፡፡ መምህሩ ዞር ሲሉ ለሷ ብቻ በሚሰማ ድምጽ «በይ በሚቀጥለው የኔም የፈተና ወረቀት እንዳይጠፋ!» ብሎ ከቢሮአቸው ወጣ፡፡ ብሌን ፈገግ አለች፡፡

የመጣችበትን ጉዳይ በማስታወስ ስለፈተና ወረቀቷ መምህሯን ጠየቀች፡፡ የፈተና ቀኑን በማስታወስ ነገረቻቸው፡፡ መምህሩ እየገባቸው ያልገባቸው መሰሉ፡፡ «ብሌን አንቺ ጉበዝ ልጅ ነሽ፡፡ መርዳት በምችለው ሁሉ እረዳሻለሁ፡፡» ጥያቄዋ አልተመለሰም፤ ደግማ ጠየቀቻቸው፡፡

«ከዚህ ልጅ ጋር ያለሽ ግንኙነት ምንድን ነው ? ብዙም ለትምህርቱ የሚጨነቅ አይመስለኝም!» አሏት፡፡

«ጥሩ ጓደኛዬ ነው» አለች በሰለቸ አነጋገር፤ ጥያቄዋን ትተው ሌላ ጥያቄ በማንሳታቸው፡፡ «በዕረፍት ጊዜሽ የተለያዩ መፅሀፍቶች ስላሉኝ ላውስሽ ፈቃደኛ ነኝ የኔ ቆንጆ! »
ብሌን ያልሰማች መሰለች፡፡

«ጭሁን አንቺን የመሰለ ቆንጆ ልጅ! ስለ ፈተና መጨነቅ አለበት? » የሞሉትን የውጤት መመዝገቢያ ቅፅ እያሳይዋት፡፡ ከጫፒባው ሠላሳ ስምንት ተፅፎበታል፤ደስ አላት፡፡
የፈተናዬ ወረቀትስ? » አለች ደግማ፡፡

«ውጤቱን ካየሽ ምን ያደርግልሻል?»

«ለሌሎቹ ሁሉ የመልስ ወረቀት ሲመለስ የኔ...» ብላ ዝም አለች፡፡

«ጭቺ የተለየሽ ስለሆንሽ ነዋ! »

በተቀመጠችበት ወንበር ጀርባ ቆም ብለው እጃቸውን ወደ ደረቷ ሰደዱ፡፡ በቅጽበት ተነስታ እጃቸውን ምንጭቅ አድርጋ አስለቀቀቻቸው፡፡

« አዝናለሁ! መምህር»

« ምን አጠፋሁ የኔ ቆንጆ? ስለምወድሽ እኮ ነው»

« እርስዎ -እኔን?»

« ምን አልሽ?» አሏት፡፡

የቢሮውን በር በኃይል ዘግታባቸው ወጣች፡፡ የመስፍን ንግግር ከሀሳቧ አነቃት፡፡
«ምን እያሰብሽ ነው?» አላት መስፍን ሞባይሉን እያስቀመጠ፡፡

«ምንም»

የብሌንን ንግግር እያሰበ «ከእጄ አታመልጪም!» በሀሳቡ፡፡ እሷም በየቦታው ያለው የሰዎች መጥፎ ባህርይ ተመሳሳይነት እየገረማት «አቤት!መስሪያ ቤትም ለካ ስንት ጉድ ይዟል ፤ጫፍ ለመውጣት ስንት መሰናክል መታለፍ ይኖርበት ይሆን?» አለች ለብቻዋ፡፡
ሁለቱም በየራሳቸው ሀሳብ እንደተዋጡ ቢሮ ደረሱ

* * * * *

የስብሰባው ሰዓት በመድረሱ አንዳንድ ሠራተኞች ወደ አዳራሹ እየገቡ ነው፡፡ ብሌን ለክፍሏ ሠራተኞች፣

« እኔ ብቻ ነኝ ቢሮ ጠባቂ!»

«ለምን ? »

« ስብሰባ አላችሁ አይደል?»

« የምን ስብሰባ!»

« በማስታወቂያ ሠሌዳው ላይ ያለውን አላነበባችሁም?»

«አንቺም እኮ የመ/ቤቱ ባልደረባ ነሽ መሳተፍ ትችያለሽ»

« መግባት እችላለሁ?»

« አዎ፡፡»

በአዳራሹ ውስጥ በትልቁ የተፃፈ ባነር ተሰቅሏል፡፡ የተለያዩ ጽሑፎች ለተሳታፊዎች ይታደላል፡፡

«ሦስት ሰዓት ተብሎ አራት ነው እንዴ የሚጀመረው?»

ይላል በሰዓቱ የተገኘው ተሰብሳቢ አጠገቡ ለተቀመጠው፡፡

« የጊዜ አጠቃቀማችን እኮ፣ ቀድሞ የመጣውን የሚጎዳ ነው»

« እውነት ነው!»አለ፣ ራሱን በመነቅነቅ፡፡

ሌሎችም እርስ በርሳቸው ስብሰባው እስከሚጀምር ይጨዋወታሉ፡፡

የኘሮግራሙ መሪ የዕለቱን ስብሰባ አስመልክተው ለታዳሚው ኘሮግራሙን በዝርዝር አቀረቡ፡፡ በመቀጠልም «የመ/ቤታችን የኤች አይ ቪ ኤድስ ግብረ ኃይል ሰብሳቢ ስለተከናወኑ ተግባራት አጭር ገለፃ ያደርጉልናል፤»በማለት ወደ መድረኩ ጋበዙ፡፡

አቶ መስፍን ወደ መድረኩ ወጥቶ ፣ «የተከበራችሁ የመ/ቤታችን ባልደረቦች ዛሬ እዚህ የተሰበሰብነው የሠራተኛውን ኃይል በማመናመን ኢኮኖሚያችንን በከፍተኛ ሁኔታ በመጉዳት ላይ ስለሚገኘው ኤች አይ ቪ ኤድስ ጉዳይ ለመወያየት ነው፡፡ በመ/ቤታችን ከግብረ ኃይሉ ጋር በመተባበር በተደረገው የፈቃደኝነት የደም ምርመራ 30% ያህሉ ተመርምረው ራሳቸውን አውቀዋል፡፡ ሌሎችም በተጓዳኝ የተከናወኑ በርካታ ተግባራት…»ብሎ በዝርዝር ተናገረ፡፡

«ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ ያልሰማ አለ ማለት አይቻልም፤ ነገር ግን በዚህ መጠን የሰማው ሁሉ አውቆአል ለማለት ግን አያስደፍርም፡፡ የበሽታውን አሳሳቢነት ተገንዝቦና አውቆ ባህሪውን የለወጠ ወይም የተጠነቀቀ ከበሽታው መዛመት ጋር ሲነፃፀር ቁጥሩ በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ሁላችንም መተኪያ ለሌላት ህይወታችን ዋጋ እንስጥ! አመሰግናለሁ፡፡» በማለት ወደ መቀመጫው አመራ፡፡

መስፍን ወደ መቀመጫው ሲመለስ፣

«ንግግር በተግባር የሚተረጎመው መቼ ነው?»

አለች ከነብሌን አጠገብ የተቀመጠችው ለጓደኞችዋ፡፡

«እንዴት?»

አለች አንዷ ቀልደኛ ከመሀል

« መስፍንን አታዩትም እንዲህ ሲደሰኩር»

« የመድረክ አንበሶች ፀባይ ነዋ! ኧረ እንደውም አንድ ታሪክ ትዝ አለኝ፡፡ ጓደኞችዋ ጆሮአቸውን ሰጥተው ያዳምጣሉ፡፡ አንዱ እንዲህ እንደ አቶ መስፍን መድረክ ላይ ጥሩ ሰባኪ ነው፡፡ ነገር ግን እቤቱ አስቸጋሪ ሰው ነበር— ንግግሩ ከተግባሩ ጋር የማይዛመድ፡፡ በመድረክ ላይ በርካታ ታዳሚዎች አሉት፡፡ በተለያዩ የማህበራዊ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ንግግር ሲያደርግ ሁሉም ፈዞ የሚያዳምጠው ነው፡፡ ባለቤቱም በአንድ ኘሮግራሙ ላይ ተገኝታ ንግግሩን ካዳመጠች በኋላ ከመድረኩ ሲወርድ እባክህን ውድ ባለቤቴ! ለአንተ ከዚህ ውጭ አይመችህም፤ ሁልጊዜ መድረክ ላይ ኑርልኝ፡፡»

አለች አሉ፡፡ የሰሙት ሁሉ ሳቁ፡፡

« ታዲያ! አቶ መስፍንም የቢሮ ሥራው ቀርቶ መድረክ ላይ ይኑር ማለትሽ ነው?»

የመጀመሪያዋ ተናጋሪ ጠየቀች፡፡

« ሌላ ትርጉም እስካልተሰጠው ያስኬዳል አለች፡፡ በድጋሚ የሳቅ ድምፅ ተሰማ፡፡

የዕረፍት ሰዓት ደርሶ ለሻይ ሲወጡ ሁሉም በየቡድን እየሆነ ይወያያል፡፡ በኘሮግራሙ መሠረት የውይይት ክፍለ ጊዜው ግብረኃይሉ ባከናወነው የሥራ እንቅስቃሴ ዙሪያ ነው፡፡ አዘጋጆቹ ለዕረፍት የተሰጠው ሃያ ደቂቃ በማለቁ ተሰብሳቢዎቹ ወደ አዳራሹ ገቡ፡፡

መስፍን ከአዘጋጆቹ ጋር መድረኩ ላይ ተቀምጧል፡፡ «ከሻይ ዕረፍት በፊት በቀረበው ዝግጅት ላይ ለመወያየት ጥያቄ ወይም አስተያየት ካላችሁ?» ብሎ እድምተኞቹን ጋበዘ፡፡ በርካታ እጆች ይታያሉ፤በየተራ ጥያቄና አስተያየት ቀረበ፡፡

«ዝግጅታችሁ ጥሩ ነው፤የተለያዩ ትምህርታዊ መልዕክቶችን በማዘጋጀት ማስተማር አለባችሁ፡፡»

ሌላም … ሌላም አስተያየት ተሰጠ፡፡

«ጥያቄ አለኝ አለ ከመሀል ከተቀመጡት አንዱ»

«እሺ ቀጥል» አለው፡፡

«ግብረ ኃይሉ በተለያዩ ሰበቦች (በደረጃ ዕድገት፣በቅጥር በመሳሰሉት) ምክንያት በእህቶቻችን ላይ የሚደርሰውን ጾታዊ ጥቃት እንዴት ለመከላከል ይችላል?»

መስፍን ለጥያቄው መልስ ለመስጠት ጉሮሮውን እየጠራረገ «ጥሩ ጥያቄ ነው ሁላችንም ለጉዳዩ የኔነት ተሰምቶን ለእህቶቻችን እንክብካቤ ልናደርግ ይገባል፡፡ እንዲህ ዓይነቱን አስነዋሪ ድርጊት የሚፈጽሙትን ለመከላከል ከመሥሪያ ቤታችን ሴቶች ጉዳይ መምሪያ ጋር ለመስራት ዕቅድ ይዘናል፡፡ ሁላችንም ለጉዳዩ ትኩረት መስጠት ይኖርብናል፤የተግባር ሰው መሆን አለብን፡፡» የዕንባ ሲቃ እንደያዘው ሁሉ ድምፁ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ቶሎ ቶሎ ይናገራል፡፡

ብሌን ይህንን ንግግር እያዳመጠች «እንዴ! እውነት የሚባል ነገር ከሀገር ሊጠፋ ነው ማለት ነው፡፡» አለች ለብቻዋ፡፡የመስፍን ንግግር ከተግባሩ ጋር አልዛመድ ቢላት፡፡

ከምሳ እረፍት በኂላ ዝግጅቱ ቀጥሏል፡፡ ስሜትን የሚነኩ ልዩ ልዩ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች፣ ድራማ እንዲሁም ተመክሮአቸውን ያካፈሉ ተጋባዥ እንግዶች ነበሩ ፡፡የዕለቱ ዝግጅት እንደተጠናቀቀ መስፍን የተመልካቹን ስሜት እያነበበ፣«አሳዛኝ ነው! በገጠር ብቻ ሳይሆን እዚሁ ከተማችን ውስጥ በተለይ በሴት እህቶቻችን ላይ የሚደርሰው ጾታዊ ጥቃት እየተበራከተ መጥቷል፤

«አሁን ስለ ሴት የሚያዝኑ አይመስሉም!ምናለ ራሳቸውን ወደ ውስጥ ቢያዩ»ትላለች ብሌን ለብቻዋ፡፡ ኘሮግራሙ በሰዓቱ ተጠናቋል፤ተሳታፊው ስለ ዕለቱ ዝግጅት እርስ በርሱ እየተነጋገረ ከአዳራሹ ወጥቶ ሄደ፡፡

* * * * *

ብሌን ልምምዷን ልታጠናቅቅ ጥቂት ቀናት ነው የቀራት፡፡ ከትምህርት ቤቷ የተሰጣትን የሥራ ላይ ልምምድ ማጠናቀቂያ ውጤት መሙያ ቅፅ ትሠራበት ከነበረው ክፍል ተሞልቶ አስተያየት እንዲሰጥና የማረጋገጫ ፊርማ እንዲፈርም ለመስፍን ተልኮለታል፡፡ መስፍን የደረሰውን ቅፅ አይቶ ብሌንን አስጠራት፡፡ ብሌን ወደ ክፍሉ እንደገባች በፈገግታ ከመቀመጫው ብድግ እያለ፣
« ከሠራተኞቹ ጋር እንዴት ነው! ከፍተኛ ውጤት ነው የሰጡሽ» ብሎ የተሞላላትን ውጤት አሳያት፡፡

« የሰጡኝ ሳይሆን ማግኘት የሚገባኝ» አለች፡፡ ለራሷ ብቻ በሚሰማ ድምፅ፡፡ ወዲያው ውጤቷን አይታ ፈገግ አለች፡፡

« ለተማሪ እንዲህ ይሰጣል!» አላት በማሾፍ ቅላጼ፡፡

« በአግባቡ ሥራውን ካከናወነ» አለች ቃላቱን ረገጥ አድርጋ፡፡

« ቀኑ እንዴት ይሮጣል! ስንት ጊዜ ሆነሽ?»

« ሁለት ወር»

ፊት ለፊት ሲያያት የውስጡን ስሜት ሊቆጣጠረው አልቻለም፤ይህንን አጋጣሚ ማለፍ አልፈለገም፤ በተቀመጠችበት ወንበር ጀርባ ተጠግቶ« የኔ ቆንጆ በደንብ ሳንጨዋወት ልምምድሽን ልትጨርሺ ነው? በማንኛውም ጊዜ እየመጣሽ መስራት ትችያለሽ መሥሪያ ቤታችን ለጉበዝ ሠራተኞች ክፍት ነው» ብሎ እጆቹን ከፀጉሯ አልፎ ወደ ጡቶቿ አስጠጋ፡፡

«አሁንም! ሁሌ በስህተት ውስጥ ማለፍ አይሰለችዎትም? አዝናለሁ! ንግግሯ ምንም አልመሰለውም »አይኑን ከአይኗ ሳይነቅል ቅር ሰሰኘሁሽ በዕረፍት ቀንሽ ብንገናኝ!» እያለ ጉንጯን በጣቱ ነካ አደረገው፡፡

«ከትዕግሥቱ በላይ አልሆኑም? አልበዛም እንዴ! ቢሮ መሆኑን እኔ ላስታውሶት!»ውጭ ብንገናኝ ያልኩሽ እኮ! ...» ቀልዱ አልተሳካለትም፡፡ በጣም ችክ ማለቱ የታወቀው አይመስልም፡፡ ብሌን ጤንነቱን ተጠራጠረች፡፡ «እርስዎ ተማሪ እኔ ደግሞ አስተማሪ የሆንኩ መሰለኝ» አለች በንዴት፡፡ ንግግሯን እንዳልሰማ

ሁሉ «ሲመችሽ ስልኬ ላይ ምልክት አድርጊልኝ» ብሎ ቢዝነስ ካርዱን የኮቷ ኪስ ውስጥ ከተተው፡፡ከመቅጽበት አውጥታ ጠረጴዛው ላይ ወረወረችው፡፡ «ምን አይነት ባለጌ ሰው ናቸው! ብላ እያሰበች ወደ ክፍሏ ልትሄድ ስትል እጇን ያዝ አድርጐ «በዚህ አይነት ፀባይ ቅፁ ላይፈረምልሽ ይችላል፡፡»አላት፡፡ «ሊቀር ይችላል በዚህ መንገድ እንዳገኝ አልፈልግም» ብላ ጥላው ወጣች፡፡

✷ ✷ ✷ ✷ ✷

በሚቀጥለው ቀን ወንድሟ ዳንኤል የሥራ ዕድገት ማግኘቱን ምክንያት በማድረግ ሊጋብዛት ፈልጓል፡፡

«ዛሬ ምሳ አብረን እንበላለን፤ በዛውም ሰው አስተዋውቅሻለሁ»

«ይመቸኛል፣ የት እንገናኝ?»

«ቢሮሽ መጥቼ አብረን እንሄዳለን፤ ካዛንቺስ ምርጥ ምግብ ቤት አለ፡፡»

«ሰውየው ባያመላልሱኝ እኮ ዛሬ ወደ ሥራ መግባት አይጠበቅብኝም ነበር»

«የሳቸው ጉዳይ ቀላል ነው! የጓደኛዬ አባት እዛ ነው የሚሠሩት»

«እውነት! ታዲያ እስካሁን ለምን አልነገርከኝም!»

«በራስ መተማመንሽን እንዳልገድበው ብዬ!»

«ክፍሌ ውስጥ ያሉት ሠራተኞች ለዋናው ኃላፊ ንገሪ ብለውኛል፡፡»

«እሱም አንድ አማራጭ ነው ቻው! ብሏት ከታክሲ ሲወርድ»

« ሰዓት ይከበር ! » አለችው፡፡

በምሳ ሰዓት በቀጠሮአቸው ተገናኝተው ወደ ካዛንቺስ ሄዱ፡፡ ሰላም ሰዓቷን አክብራ ተገኝታለች፡፡ እንደደረሱ ዳንኤል እህቱን ከጓደኛው አስተዋወቃቸው፡፡

«ብሌን »

«ሰላም» ተሳሳሙ፡፡

«በጣም ነው የምትመሳሰሉት!» አለችው፡፡ ሰላም

«አዎ፤ ብዙ ሰው ይለናል፡፡»

ወደ ኮረኮንቻማው መንገድ ሲታጠፉ በርካታ መኪናዎች ተደርድረዋል፡፡ዳንኤል እህቱን

«የቅፁ ጉዳይ እንዴት ሆነ? አላት፡፡ ለጥቂት ደቂቃ ዝም ብለው ስለነበር ፀጥታውን ለመስበር፡፡

«ኃላፊው ቢሮ ከሰዓት ልገባ ነው»

« ጠዋት አታስጨርሺም ነበር?»

« ስብሰባ ነበራቸው፡፡»

ሰላም ጣልቃ ገብታ «ዳኒ ነግሮኛል ስንት አይነት ባለጌ አለ! ለፋዘር ማታ እነግረዋለሁ»

« የኃላፊውን መልስ ሰምቼ ትነግሪያቸዋለሽ!»

ወደ ሰፊው የምግብ አዳራሽ ሲገቡ የቡናው ሥነሥርዓት ልዩ ውበትን አጐናጽፎታል፡፡ አስተናጋጆቹ ከወዲያ ወዲህ ይሯሯጣሉ፡፡ በርካታ ተመጋቢዎች ነው ያሉት፡፡ ኢትዮጵያውያን፣ የውጭ አገር ሰዎች፡፡ አስተናጋጁ መቀመጫ እያሳያቸው በዳር በኩል ተቀመጡ፡፡ ዳንኤል « የአለም የምግብ ቀን የሚከበር ይመስላል! » ሲል እነብሌን ሳቁ፡፡

ከቤቱ ውጭ በልዩ ቀለማት የተወጠረው ሸራ ለምግብ ቤቱ ልዩ ድምቀትን ሰጥቶታል፡፡ ነፋሱ ቀዝቃዛ አየር ስለሚያመጣ ውጭ የነበረውን ሙቀት አያስታውስም፡፡ ያዘዙትን ምግብ በፈገግታ የታጀበው አስተናጋጅ ይዞላቸው መጣ፡፡ እየተጎራረሱ መብላት ያዙ፡፡

ከቀረበው ቡና ዳንኤልና ሰላም አዘው ጠጡ፡፡ ሂሳብ ከፍሎ ወደ መታጠቢያው ሲሄዱ ብሌን የጓደኛዋን እህት አይታ ለሰላምታ ወደ ኋላ ቀረች፡፡ ሰላምና ዳንኤል እጃቸውን ታጥበው ሲመለሱ « ከልጆቻችን ጋር እንጋፋለን ! » አለ ሰላምን እየተመለከተአቶ መስፍን ፡፡

ሰላም ደንገጥ እንደማለት ብላ አባቷን አየችው፡፡ ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም ብላ ቆየችና

«አንድ መ/ቤት ነው የምንሠራው» አለች ወደ ዳንኤል እያመለከተች፡፡

«መስፍን»

«ዳንኤል» ተጨባበጡ፡፡

ሰላም ብሌንን ስታያት ሰላምታዋን አልጨረሰችም፡፡ ለአባቷ ጉዳዩን ልትነግርላት ቸኩላለች፡፡ የሰላም አባት እነዳንኤልን

« ልሸኛችሁ ? » አለ ፈገግ ብሎ፡፡

« እሺ! »አለች ሰላም ፈጠን ብላ፡፡

አቶ መስፍን መኪናውን ለማዞር ከጓደኛው ጋር ቀድመው ወጡ፡፡ ብሌን ስትመጣ ሰላም፣

« ፋዘርን አገኘነው፤ ጉዳይሽንም ትነግሪዋለሽ» አለቻት፡፡

« የት ናቸው ? »

« ቀዩ ዲ ኤክስ ውስጥ»

ሦስቱም ተያይዘው ወደ መኪናው ገቡ፡፡

« አባቴን ተዋወቂው » አለች ፈገግ ብላ፡፡

«አውቃቸዋለሁ!» ብሌን በድንጋጤ መልስ ሰጠች፡፡

መስፍን ቀልጠፍ ብሎ «እኛ ጋ ነው የምትሠራው፣ ጎበዝ ልጅ ናት፡፡ አለ፤ለመረጋጋት እየሞከረ

«ትተዋወቃላችሁ ? » አላት ሰላምን፡፡

« አዎ ! የዳንኤል እህት ናት ፤» ብሌንን እየተመለከተቻት «ነገሪው እሱ ያስጨርስልሻል፤» አለች በመተዋወቃቸው ደስ ብሏት፡፡ ብሌን ራሷን ነቀነቀች፡፡ ዳንኤልና ብሌን ተያዩ፤ መስፍን ፊትለፊት በመስታወት ተመለከታቸው ፡፡ ዳንኤል እህቱ ስለመስፍን ስለምትነግረው ስሙን ያውቃል፡፡ ነገር ግን የሰላም አባት ይሆናል ብሎ አልጠረጠረም፡፡ ብሌን ሰላምን ጠቀስ አደረገቻት፡፡ ዝም በይ! እንደማለት ብላ፡፡

ሰላም የጉዳዩ ባለቤት የአባቷ ጓደኛ ይሆናሉ ብላ ዝም አለች፡፡ መ/ቤቷ ስትደርስ ከዳንኤል ጋር አመስግነው ወረዱ፡፡ ለወሬ ጥድፍ ብላ « የፋዘር ጓደኛ ናቸው ብሌንን ያስቸገሯት?» ዝም አለ ዳንኤል፡፡

«ዳኒ ! »አለች፡፡

ጓደኛውን ያፈቅራታል፤ሊያሳዝናት አልፈለገም ሳይወድ በግዱ«አዎ» አላት ስህተቱ የአባቷ ጓደኛ እንደሆነ ሁሉ፡፡

ብሌን መመላለሱ ስልችት ብሏታል፡፡ ወደ ዋና ኃላፊው ቢሮ ለመሄድ ስትዘጋጅ ከመዝገብ ቤት በፖስታ የታሸገ ደብዳቤ የያዘች ሠራተኛ ለብሌን ፖስታውን ሰጥታት በማስፈረሚያ ቅጽ ላይ አስፈረመቻት፡፡

«ምንድነው» አለች

«ለት/ቤትሽ የተሞላልሽ ቅፅ»

«አመሰግናለሁ፡፡»

ክፍሏ ውስጥ የሚገኙትን ሠራተኞች ፖስታውን እያሳየቻቸው «ከነገ ጀምሮ ሠራተኛነቴ አበቃ፤ ወደ ትምህርት ቤቴ እመለሳለሁ፡፡ እስካሁን ላደረጋችሁልኝ ትብብር አመሰግናለሁ፡፡ ጥሩ ሰዎች በመሆናችሁ እወዳችኋለሁ፡፡»

«እኛም ጠንካራ በመሆንሽ እንወድሻለን!» አሏት፡፡

«አቶ መስፍንንም ስለ ሁሉም ነገር ተሰናበቺው!» አለች ከጥግ የተቀመጠችው፡፡

«ስለ ጥሩ አመለካከትሽ አመሰግናለሁ ግን ያስፈልጋል?»

ወደ ቢሮው ገብታ «አመሰግናለሁ ደህና ሁኑ!» አለችው፡፡ በዝምታ ሲያያት ቆይቶ፣

« ብሌን እንዴት ጠንካራ ልጅ ነሽ?በአንቺ ጥንካሬ ውስጥ ባዶነቴን አየሁት፡»አላት ትክዝ ብሎ

« ከስህተት መማር ከየትኛውም ጥንካሬ ይበልጣል» አለችው፡፡

« ‘ጫፍ ላይ የወጣ ሁሉን ያያል!’ነበር ያልሽኝ?»

« ትክክል የቀረኝ መንገድ ከመጣሁበት ይረዝማል ጫፍ ለመውጣት ግን ጉዞው እንደምናስበው ቀላል አይደለም»ንግግሯ ጠጠረበት፡፡

«በርቺ! እኔ ግን ዛሬ በልጄ ፊት ታች ወረድኩ፡፡»

የእርስዎ ፀፀት በቂ ነው፤ወደ ቤተሰብ ይሻገራል ብለው ግን አይስጉ፤ለነገው ትክክለኛ አቋምዎት ለራስዎ ቃል ግቡ፡፡»

«እውነትም ቦታ ተለዋውጠናል!» አለ በውስጡ በተናገረችው ሀሳብ ጥንካሬ እየተገረመ፡፡

«ብሌን!መልካም የትምህርት ጊዜ፣ ሀሳብሽ እንዲሳካ ከልብ እመኝልሻለሁ ብሎ በመስኮቱ በኩል ወደ ውጭ ይመለከት ጀመር ፡፡

«ደህና ሁኑ!» ተሰናብታው ወጣች፡፡

አልሰማትም፡፡ በሀሳቡ ሩቅ ነጒደ፡፡`

The National Bank of Ethiopia Commitment

From the Ethics Office of the Bank

“The Bank recognizes its obligation to the Country, Government, staff, Financial sector, the community, and other stakeholders to encourage and maintain the highest ethical standards. Therefore, ethical behavior and leadership is expected of every employee at the Bank. This refers not only to knowledge about laws, rules, policies and procedures that are applicable to your job, but promoting the highest standards of professionalism and ethical conduct throughout the Bank....Ethics go beyond the law and regulations.”

What is Ethics?

Ethics – the discipline dealing with good and bad, right and wrong or moral duty and obligation.

Ethics – a concept of right and wrong conduct.

“Ethics is knowing the difference between what you have a right to do and what is the right thing to do.”
-Potter Steward, former Supreme Court Justice

Some Ethics Terminology

Ethical principles – guides to moral behavior

Ethical relativism – Ethical principles are defined by
Periods of time in history
A society’s traditions
The special circumstances of the moment
Personal opinion
Thus there may be no universal set of ethics, but it is a universal human trait.

Ethical egoist – Person who puts his/her own selfish interests above all other considerations, denying the ethical needs and beliefs of others

Ethics and Business

Business ethics – application of general ethical ideas to business behavior but NOT a special set of ethical ideas.

Ethical climate – Unspoken understanding among employees of what is and is not acceptable behavior....part of corporate culture. Tone at the top must support ethical climate!

Ethical charismatic leader – exhibits strong moral character and is capable of positively influencing entire organization. Often seen as other-centered visionaries who bring out the best in others.

Ethics is more than compliance

Compliance is doing what you are required to do by laws or rules. It's a baseline…the minimum.
Ethics is about doing what you should do because it is right.

Ethical Dilemmas

Ethical dilemmas – facing alternatives…each with compelling reasons for choosing.

Ask these questions:
Is it legal?
Is it right?
Who will be impacted?
Does it fit the organization's values?
How will I feel afterwards?
How will it look in the newspaper or other media?
Will it reflect poorly on the organization?
If you don't know, ask somebody.

Challenges to Achieving Ethical Behavior
Recognizing there IS an ethical issue.
Figuring out the right thing to do.
Knowing the right thing to do and not having the courage to do it.
Realizing that doing the right thing many not always guarantee a "good" outcome in the short term.

What's the Point?
Basic assumption: Our Bank, staff and administration are ethical.

Someone who is basically unethical is probably not going to be swayed by any amount of ethics "training".

So why bother?
Just remember….
Compliance is about doing what you are required to do by laws or rules.

Ethics is about doing what you should do because it is right!

An ethical person chooses to do more than the law requires and less than the law allows.
-Christopher Stone

(እንተሳለፍ)

ፍቅርና ተስፋ .... ሰንቆ ለመኖር
ቤተሰብ ጓደኛ .... አብሮነት እንዲሰምር
ትዕግሥት እንድታብብ .... በልብህ ማኀደር
እርጋ በሕሊናህ .... በዘመናት ቀመር፡፡

የምኞት ፈረስህ .... በትዝታ ሲከንፍ
ሲያደርስህ ሲፈጥን .... ከዳንኪራው በራፍ
በሀራራው ሰዓት .... በሱሶቹ ምዕራፍ
ግራውን ሲያሳይህ .... አንተ በቀኝ እለፍ፡፡

ድንገት ብትሰማ .... ያሉባልታ ዜና
ከብስጭት እሳት .... ከሀዘን ደመና
እለፈው ይለፍህ .... አዕምሮ ግዛና
በእውነት ትስቃለህ .... ውሸት ታፍርና፤፡፡

ሀሣብህ አያረግዝ .... ቅጽበታዊ ቅናት
ቱግ ባይ ስሜትክን .... ከአፍንጫህ አርቃት
ያልታሰበች ነገር .... ያቺ ትንሽ እሳት
ታጠፋለች ተስፋ .... ተለኩሳ ድንገት፡፡

ንዴትህን አብርዳት .... ለትዕግሥትህ ካሳ
ሕሊናን ለማዳን .... ከፀፀት ጠባሳ
ራስክን አታኩርፍ .... አትጋጭ ከሰው ጋር
ደቂቃዋ ስታልፍ .... ትመጣለች ፍቅር፡፡

እሽትና ቆንጆን .... አይተህ ካለለፍካት
በቅጽበት ችኮላ .... ቀጥፈህ ከቀመስካት
ትቆርጣለህ ትኬት .... ቀንጥሰህ ከጣልካት
ግራ ቀኝ ሳታልም .... ሳታሰብ አድርገህ
(ማኖ) እንዳትነካ .... ምኞትህ አታሎህ
ተሳለፍ መንገዱን .... ለሰኮንዶች ቆመህ፡፡

ጉም የዘገነና .... አንድ ሃሣብ ያመነ
ይኖራል ዘወትር .... ሁሌ እንደባነነ
በምታየው ሕልም .... በሸፈነው ቅዠት
በሌሊት ሳትቸኩል .... አጢነው በንጋት
የረጋ ወተት ነው .... ቅቤ የሚያድለው
ማርና ሰም መፍቻው .... ቀንና ቅኔ ነው፡፡

ውሳኔህ እንዳይሆን .... የምኞት እንጥልጥል
ትዕዛዝህ አይክረር .... ውሃ ቀጠነ አትበል
ይለፍህ እለፈው .... ስከን እንደቡና
የጥበብ ቅመሙ .... ማስተዋል ነውና፡፡

ሕይወት አደብ ገዝታ .... ለመኖር በፀጋ
ለደቂቃ አጢናት .... የትዕግሥትን ዋጋ
ያቺን አጭር ሰኮንድ .... ሚጢጢዬ ጊዜ
እስኪያልፍ እንለፋት .... የያዘን አባዜ፡፡

በቀለ መንግሥቴ (ኢብባ)

Frequently asked questions (FAQ) about the activities of the Bank

1. **Does NBE provide loan?**
NBE as a central bank, does provide loan to the government and banks, not to individuals and business entities.

2. **What is the current deposit interest rate?**
NBE has set the minimum saving and time deposit rates at 4%. But banks may pay higher than this rate.

3. **What is the lending rate of Banks?**
The lending rate is fully liberalised, and hence there is no lower/upper lending limit rate in the country. Each bank determines the lending rates.

4. **Can any one participate in the auction of Treasury Bills?**
Yes, with the minimum amount of Birr 5000.

5. **Can I get a foreign currency to pay for education, subscriptions, health, etc?**
All eligible individuals can get foreign currency from commercial banks for these and other purposes.

6. **How many banks, insurance companies and microfinance (MFIs) organizations operate in Ethiopia?**
There are 8 private and 3 government-owned banks, 9 private and 1 government owned insurance companies, and 28 MFIs (as of October 2007).

7. **What are the Ethiopian currency denominations?**
Ethiopia has 1, 5, 10, 50 and 100 birr notes and a 1, 5, 10, 25, 50 cents coins.

8. **Which commercial bank, insurance company or MFIs is trust worthy to deal with?**
All are trust worthy and working as per the close inspection and guidance of NBE.

9. **Who is illegible to engage in the business of banks, insurance and MFIs?**
Only Ethiopians can own and operate financial institutions.

10. **Can I exchange foreign currency to birr in banks?**
Yes.

11. **What are the major foreign currencies that the country uses?**
US Dollar, Pound Sterling and Euro are vastly used in Ethiopia. However, Banks in Ethiopia transact in Japanese Yen, Rand, Rupee, Swedish Krona, etc.

12. **Is the birr vulnerable to counterfeit, as other currencies do?**
All currencies are venerable to counterfeit. Hence you need to know your currency's security features in order to combat counterfeit.

13. **What should I do, If I find a counterfeit?**
You should immediately report the case to the police.

14. **Can I use a credit card in Ethiopia? Which types of credit cards are used in the country?**
Yes. But only few places give credit card services for customers. Since 2006, Domestic banks have also started to issue credit cards and one can use these credit cards. In Ethiopia: American Express, Master, Visa, Diners Club and Cart Blanche, and Euro cards are used.

15. **Is it possible to transact in foreign currency?**
Only certified hotels, duty free shops, immigration offices, Civil Aviation Authority, and airline ticket offices are entitled to accept payments in foreign currency.

16. **Can I deposit a foreign currency in my account?**
All Ethiopian nationals living and working abroad and non-resident foreign nationals of Ethiopian origin can open fixed (time deposit), current and non-repatriable Birr accounts in commercial banks.